# የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን

የ2017 በጀት ዓመት የ2ተኛ ሩብ ዓመት የክንውን ሪፖርት

ታህሳስ /2017

ኢግባ አዲስ አበባ

**ደርሞ**

*የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የግብርና ምርቶችን፣ግብዓቶችንና ፣ አገልግሎቶችንና የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቁጥጥር ስራዎችን እንዲያከናውን ስልጣን የተሰጠው የግብርና ቁጥጥር ተቋም ነው፡፡ ባለስልጣኑ በሁለት ዋና ዋና የቁጥጥር ፕሮግራሞች ማለትም በዕጽዋት ቁጥጥር ዘርፍ እንዲሁም በእንስሳት ቁጥጥር ስር ባሉ ክፍሎቹ የተደራጀና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚሄድ የቁጥጥር ተግባራትን እያከናወነ ሲሆን ከነዚህ ዘርፎች በተጨማሪም የግብርና ሜካናይዜሽን ፣ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ቁጥጥር ስራ ለማስጀመር እየሠራ ይገኛል ፡፡ ይህ የሪፖርት ሰነድ በተለይም የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ መሠረት ባደረጉ የቁልፍ ተግባራት አመልካቾቸ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ  የሪፖርት አጠቃላይ የግብርና ሴክተር ሪፖርት አካል ሲሆን በመጀመሪያዉ ሩብ ዓመት  በሁሉም ዘርፍ ታቅደው የተከናወኑ ቁልፍ አመልካች አፈጻምን የሚያሳይ ነው፡፡ ለአብነትም አበይት ከሆኑ ክንውኖች መካከል የአበባን እርሻ ወደ ዓለማቀፍ ስታንዳርድ ለማስገባት እየተክናወኑ ያሉ የክትትል ስራዎች፣የምርቶችን ጤንነትና ጥራትና ደህንነት ለማስጠበቅ የተክናውኑ ተግባራት ማለትም 33145 ሚትሪክ ቶን የመግቢያ ፍቃድ የመስጠት እንዲሁም ለ6 ፀረ ተባይና ማዳበሪያ አዳዲስ ተቋማት በምዝገባ መስፈርቱ መሰረት መመዝገብ እና የብቃት ማረጋገጫ የመስጠት ሰራ ተከናውኗል፡፡ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ እጽዋትና የእጽዋት ዉጤቶች የቅደመ ማስገቢያ ሰርተፊኬት ፣ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቶችን መስጠት እንዲሁም ነባሮችን የማደስ ስራ ተካሂዷል፡፡በእንስሳት ሬጉላቶሪ ዘርፍም ለ100000 ሺህ የቁም እንስሳት (ዳልጋ ከብቶች፣ ግመል፣ በግና ፍየሎች) በኳራንቲን ጣቢያዎች ውስጥ በማቆየት አስፈላጊውን ክትባት፤ የጤና ምርመራ አድርገው የኳራንቲን ጊዜ ለጨረሱ ለ1171022 ሺህ የቁም እንስሳት አለም አቀፍ የጤና ሰርተፍኬት በመስጠት ወደ ተቀባይ ሀገሮች እንዲላኩ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም 1854 ቶን የእንስሳት መድኃኒት ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ጥቅም ላይ እንዲውል    መደረጉ ይገኑበታል፤ ከዚህ በተጨማሪም የኤክስፖርት ቄራዎችን ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑና በተለይም ወደ ቻይና ገበያ እንዲገቡ የሚያስችል ፍተሻ በራሳቸው በኩባንያዎቹ የተደረገ ሲሆን ቄራዎችም በተሰጣቸው የማስተካከያ ግብረመልስ መሠረት የጎደላቸውን እንዲያሟሉ (ማሰስተካከያ እንዲያደርጉ ) ምክረ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡*

*ከላይ ጠቅለል ብሎ የቀረበውን በየዘርፍፎቹ ከተከናውኑ ስራዎች ብማክናውን ሂደት፣ የበጀት እጥረት ፣ የተሽከረካሪና ሌሎችም ችገሮቸ ያጋጥሙ ሲሆን በአፈጻጸም ሪፖርቱ መሠረት በማድረግ ታቅደው የተከናዋኑትን ቁልፍ አፈጻጸም ሥራዎችን በሁሉም ዘርፎች በየድርሻቸዉ በዝርዝር ቀርቦ ዉይይት የተደረገበት ሲሆን የነበሩ ጠካራ ጐኖችን አጠናክሮ በመቀጠል ፣የታዩ ክፌተቶች ላይ በቀጣዩ ሩብ ዓመት ወይም ትኩረት ሰጥቶ በመተግበር የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ ከዚህ በላቀ ሁኔታ የሚከናወን ይሆናል፡፡*

# ማውጫ


መግቢያ ........ 3

i. የሪፖርቱ አስፈላጊነት ........ 4

ii. የሪፖርቱ መነሻ ........ 4

iii. የባለሰለጣኑ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች ........ 4

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 በጀት አመት የ2ኛ ሩብ አመት ሪፖርት ........ 7

1. የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴሽን እና መካናይዜሽን ሬጉሊቶሪ ........ 7

2. የእጽዋት ግብዓቶች ምርቶች እና start-ups አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር ........ 7

2.1 የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ቁጥጥር ........ 7

2.2 ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች ........ 9

2.3 የእፀዋት ዝርያ ጥበቃና ዘር ጥራት ቁጥጥር ........ 11

3. የእንሰሳት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር ........ 13

3.1.የእንሰሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ ........ 13

3.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ ወደ ውጭ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ........ 14

3.3 የእንሰሳት መድሃኒት ጥራት ደህነነትና ፈዋሽነነት ማረጋገጥ ........ 15

3.4 ጥራትና ደህነነቱ የተረጋገጠ የእንሰሳት መኖ ........ 17

3.5 ደረጃውን የጠበቀ የእንሰሳት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት ........ 19

4. የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር ........ 20

4.1 በስልጠና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር ........ 20

4.2 ተግባራዊ የተደረገ የህግ ማዕቀፍ ........ 25

4.3 በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (Digitalization) የታገዘ አገልግሎት ........ 27

መረጃ ማጠናከር ........ 28

ያጋጠሙ ችግሮች ናየተወሰዱ መፍትሔዎች ........ 48

ያጋጠሙ ችግሮች ........ 48

የተወሰዱ መፍትሔዎችና ምክረ ሀሳብ ........ 50

4. የ2017 የ2[ተኛ]ው ሩብ ዓመት የበጀት አፈጻጸም ........ 52

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 2ኛ ሩበ ዓመት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት በቁልፍ አመልካች ........ 54

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በ2021 በፌዴራል ፓርላማ በአዋጅ ቁጥር 1263/2021 አንቀጽ 11 ላይ በመመስረት ስልጣኑ እና ሚናው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 509/2022 ተለይቷል፡፡ ባለስልጣኑ በዋናነት የቁጥጥር ተግባራት መሠረት በማድረግ በዋና ዋና ምርቶችና አገልግሎቶች ማለትም የግብርና ቴክኖሎጂዎች፣ የግብርና ግብአቶች፣ የግብርና ምርቶች እና የግብርና አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ፣ የተመዘገቡ እና የምስክር ወረቀት ብቃት ባለው ሰው የሚመሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ የግብርና ምርቶች እና አገልግሎቶች የአፈጻጸም/ውጤታማነት፣ የጥራት፣ የጤና እና የደህንነት ደረጃዎችን የሚያከብሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተከታታይ ምርመራዎችን ያደርጋል እንደ አስፈላጊነቱ የቁጥጥር እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

የኢትዩጰያ ግብርና ባለስልጣን በ10 አመት እና በመካከለኛ ዘመን እቅዱ ጋር በማጣጣም እንዲሁም የግብርና ግብዓትና ምርቶችን ከመቆጣጠር አኩያ ከግብርና ሚኒስቴር የመካከለኛ ዘመን ስትራቴጂክ እቅድ ጋር በማጣጣም ፣ የ1 ሩብ አመት ያለውን አፈፃፀም ፣ጥንካሬ እና ድክመትን መሰረት በማድረግ ክፍተቶችን በማየት በተጨማሪም፣ የእቅዱን አፈፃፀም አወንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ በመለየት ይህንን የ2017 በጀት አመት እቅድ  በማዘጋጀት ወደ ሥራ የገባ ሲሆን ይህንን እቅድ ተግባራዊነት ለመከታተል የሚያስችል የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ ከሚከተታተልበት መንገድ ውስጥ በየሩብ አመቱ የሩብ አመት የአፈጻጸም ሪፖርት ማድረግ አንዱ ነው ይህንንም መሠረት በማድረግ የተቀመጡትን የባለስልጣኑን ግቦች መሠረት በማድረግ በ2017 በጀት አመት የ2ተኛ ሩብ አመት በየዘርፉ የተከናወኑና በቁልፍ አመልካቾች ላይ የተመሠረተ የአፈጻጸም ሪፖርትን እንደሚከተለው ተጠናቅሯል፡፡

## i. የሪፖርቱ አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ ግብርናባለስልጣን በየጊዜው ሊለካ የሚችል ግብ በማስቀመጥ በ10 አመት እንዲደርስበት የታቀደው ግብ ላይ ለመድረስ በየአመቱ ዕቅዱ ን ሊፈጸም በሚችልና አሳታፊ በሆነ መልኩ አቅዶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል በዚህም መሠረት ፡-

- በሩብ አመቱ የታቀዱ ሥራዎችን የሚገመግምበትና ባለሰልጣኑ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ
- በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ያሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለመለየት፣
- የእርስ በርስ መማማር ለመፍጠርና ለባለድርሻ አካላት ወቅታዊና ተገቢ የሆነ መረጃ ለመሰጠት ነው፡፡

## ii. የሪፖርቱ መነሻ

ባለስልጣኑ በ2017 በጀት ዓመት ላስቀመጠው ግብ ስኬት እንደመርህ የያዘው ከዚህ በፊት ያጋጠሙ ችግሮችና እና መልካም እድሎችን በሚገባ በመፈተሽ፣ ዕቅድን አሳታፊ በማድርግ፣ ሪፖርቶች ግልጽ እና ዉጤታማ እንዲሆኑ ሲሆን ይህ ሪፖርት በዋናነት እንደመነሻ አድርጉ የያዘው

- የግብርና ሚኒስቴር የ10 አመት እና የመካከለኛ ዘመን እቅድ
- የባለስለጣኑ የ2017 በጀት አመት እቅድ እንዲሁም
- የባለስልጣኑን የ2017 1ሩብ አመት አፈጻጸም ሪፖርት፡፡

## iii. የባለሰለጣኑ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶቸ

**ተልዕኮ**

- የግብርና ቴክኖሎጂ፣አገልግሎቶችን ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ደህንነት፣ፍቱንነት፣ ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤መልካም ስም ያለውና ፣ ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓትን በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የግብርና ምርቶችን የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኤኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት፡፡

## ራዕይ

- በአለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም መሆን

## እሴቶች

- ታማኝነት /Loyalty/
- ሚስጥር ጠባቂነት /Confidentiality/
- አገልጋይነት /Commitment/
- የህግ የበላይነት /Rule of the law /
- ተጠያቂነት /Accountability /
- ደንበኛ ተኮር አገልግሎት /Customer focus/
- አለማዳላት /Impartiality /
- ትብብር /Partnership /
- ግልጽነት /Transparency/
- ምላሽ ሰጪነት /Responsiveness/

## የባለስልጣኑ ስትራቴጅክ ግቦችና/ፕሮግራሞች

**ቁልፍ ተግባራት**

### ውጤታማነቱ፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ

- ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ
- በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴንሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

### የእፀዋት በዕጽዋትና ፣ከእፀዋት ጋር በተገናኙ ግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ማጠናከር

- ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ
- ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች
- የዕጽዋት ዝርያ ጥበቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር
- ደረጃውን የጠበቀ የእፀዋት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት

### የእንስሳትና ከእንስሳት ጋር የተገናኙ የግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ቁጥጥር ማጠናከር

- የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ
- በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች
- ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት
- ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ
- ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት

### ተቋማዊ የመፈፀም አቅም ግንባታ፣ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምና አገልግሎት አሰጣጥ እና የህግ ማዕቀፎች

- የአቅም ግንባታ ሥራዎች
- የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት ማሻሻል
- የሃብት አጠቃቀምን ማሳደግ እና ሃብት ማፈላለግ
- የእቅድ ክትልና ግብረ መልስ ሥራዎችን ማከናወን
- ተቋማዊ አገልግሎትን ማሻሻል
- ሥርዓተ ጾታና ማህበራዊ አገልግሎት መተግበር
- ተቋማዊ ዲጅተላይ"ዘሽን አገልግሎት መስጠት
- ተቋማዊ ሪፎርም አተገባበር
- አጋርነት እና ህዝብ ግንኙት
- ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና

# የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 በጀት አመት የ2ኛ ሩብ አመት ሪፖርት

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የዕቅድ ስርዓት በመካከለኛ ዘመን የግብርና ሴክተር በያዘው ዕቅድመሠረት በማድረግ የሚከናወኑና በ4 ፕሮግራሞች ፣በ9 ስትራቴጂክ አላማዎች እንዲሁም እነዚህን ስትራቴጂክ አላማዎች ለማሳካት በሚከናወኑ 39 ቁልፍ አመልካቾች የተመሠረተ ነው ::ይህንን መሠረት አድርጎም የባለስልጣኑ የ2017 2ኛ ሩብ አመት ሪፖርት በፕሮግራሞች በስትራቴጂክ አላማዎች እንዲሁም በቁልፍ አመልካቾ ላይ መሠረት ያደረገ ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 1. የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴሽን እና መካናይዜሽን ሬጉሊቶሪ

የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቁጥጥር ማጠናከር

**ውጤታማነቱ፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ**

- የስራ ዘርፉ አዲስ የተደራጀ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የሬጉላቶሪ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል የቅድመ-ዝግጅት ስራዎችን ማከናወኑ ወሳኝ በመሆኑ ሁለት የአሰራር መመሪያዎችን በየደረጃው በማስገምገም ለማጸደቅ ታቅዶ የመመሪያዎቹን የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ ላይ የማስተካከያ ስራዎችን በማከናወን ለሕግ አስተያየት እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡
- በብሔራዊ የግብርና ሜካናይዜሽን ፎረም፣ እንዲሁም በሶስት ክልሎች ማለትም በኦሮሚያ፣ በሲዳማ፣ እንዲሁም በአማራ ክልል የግብርና ሜካናይዜሽን ፎረሞች ላይ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዓላማ፣ ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም በረቂቅ ደረጃ የሚገኙትን መመሪያዎችን በሚመለከት ለፎረሙ ተሳታፊዎች ገለጻ ተደርጓል
- በብሔራዊ ደረጃ በመዘጋጀት ላይ ባለው የባለብዙ ተዋንያን ኤክስቴንሽን አዋጅ ዝግጅት ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡

## 2. የእጽዋት ግብዓቶች ምርቶች እና start-ups አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር

### 2.1 የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ቁጥጥር

**ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ ተባይ**

- ባለፉት ስድስት ወራት ለ46,399 ሚትሪክ ቶን ፀረ ተባይ የመግቢያ ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ58,274 ሜትሪክ ቶን ፀረ ተባይ የፍቱንነት፣የደህንነትና የጥራት ማረጋገጥ ስራዎችን በማከናወን የመግቢያ ፍቃድ የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡

በዝርዝር ከተከናወኑ ተግባራት መካከል

- ደህንነታቸው፣ ፍቱንነታቸው እና ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ ፀረ ተባይ በቅድመ-ምዝገባ ስራዎች ለማረጋገጥ ሲባል የመስክ የሙከራ ሰነድ መገምገም እና ፈቃድ መስጠት በቁጥር 60 ታቅዶ ለ 77 (100) የፀረ ተባይ የሙከራ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡
- በፀረ-ተባዮችን ፍቱንነት ፣ ደህንነት እና ጥራት አረጋግጦ ለመመዝገብ እንዲቻል የቅድመ ምዝገባ መስፍርቶቹን ያሟሉ 79 የፀረ ተባይ ዶሴሮችን (dossier)ለመረከብ በዚህ በሩብ ዓመት ታቅዶ 93 (100) ቅበላ/መረከብ ስራ ተካሂዷል፡፡
- ለ65ዶዚየሮች የቴክኒክ ግምገማ ማከናወን በእቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን ለ 84(›100%) ዶዜየሮች የቴክኒክ ግምገማ ተደረጓል፡፡ 66 የፀረ ተባይ ዶዜየሮች የምዝገባ ሰርተፊኬት ለማዘጋጀት እና ለመመዝገብ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን ለ 82 (100) የፀረ-ተባዮች ተመዝግበዋል፣ አፈፀፀሙም 100% በላይ ሆኗል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሩብ ዓመቱ የተመዘገቡ የፀረተባይ ወቅታዊ ለማድረግ ታቅዶ የምዝገባ ዝርዝር ወቅታዊ ተደርጓል፡፡
- ለ32 የተመዘገቡ ፀረ ተባዮችን ዕድሳት እና ማሻሻል ለማከናወን ታቅዶ ለ 37(›100%) የአገልግሎት ዘመናቸው የተጠናቀቀ ፀረ ተባዮች መሻሻያ ተደርጓል፡፡

**ጥራቱ የተረጋገጠ ማዳበሪያ**

- ባለፉት ስድስት ወራት ለ1,125,558 ሚትሪክ ቶን ፀረ ተባይ የመግቢያ ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ772,497 ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ የጥራት ማረጋገጥ ስራዎችን በማክናወን የመግቢያ ፍቃድ የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡

**የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች**

- ለ127 አዳዲስ የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ተቋማት በምዝገባ መስፈርቱ መሰረት መመዝገብ እና የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ 177 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡

**በአከባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ**

- ባለፉት ስድስት ወራት አንድ በአከባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ የሚያስችሉ ጥናት ለማድረግ ታቅዶ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡

**የተወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች**

- የ13 ማዳበሪያዎች ናሙናን ከተቋማት በኢንስፔክተሮች በማስወሰድ ፣የላቦራቶሪ ፍተሻ በማስደረግ እና ከወጣ የኢትዮጵያ ደረጃ ጋር የማመሳከር 12ቱ ናሙናዎች (91.7%) የኢትዮጵያ ደረጃን ስለማያሟሉ ተቋሚቱ የብቃት ማረጋገጫቸውን እንዳያሳድሱ እንዲሁም አዳዲስ አመልካቾች ምርታቸው እንዳይመዘገብ ተደርጓል፡፡
- ከአርሲ ዞን ፖሊስ መምሪያ የወንጀል ምርመራ ዋና ክፍል በአካባቢው ሲዘዋወሩ የተያዙ ፈሳሽ ማዳበሪያዎችን በተመለከተ የማዳበሪያ ስያሜን፣ የብቃት ማረጋገጫን እና የ

ምዝገባ መረጃ ህጋዊነትን በተመለከተ በተለያየ ጊዜያት ለቀረቡ ሶስት ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል።

## 2.2 ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች

- በዚህ 6 ወር ወደ ዉጪ ሀገር ለሚላክ የጥራጥሬ እህሎች'የቅባት እህሎች' የብርዕ እና አገዳ እህሎች 'የቡና ምርት 'የአበባ ምርት' አትክልትና ፍራፍሬ ምርት' ቅመማቅመም ምርት እንዲሁም ሌሎች የግብርና ምርቶች ላይ ተገቢውን ኢንስፔክሽን ወይንም ምርመራ ለማካሄድ 430,000 ቶን ታቅዶ ክንዉን 456,477 ቶን (106%) ምርት ወደ ተለያዩ ሃገራት እንዲላክ ተደርጎል።

**በዝርዝር ከተከናወኑ ተግባራት መካከል**

- ወደ ውጪ ለሚወጣ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶችና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች የማጠንት /Fumigation ህክምና ሲካሄድ ክትትል ለማድረግ በዚህ ሩብ ዓመት150,000 ቶን ታቅዶ ክንዉን 138,403 ቶን (92%) ምርት ከተባይ ነፃ በማድረግ ወደ ተለያዩ ሃገራት መላክ ተችሏል።
- ወደ ውጪ ለሚወጣ የዕፅዋት የጤንነት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት በዚህ ሩብ ዓመት በቁጥር 25,000 ለመስጠት ታቅዶ ክንዉን 31,038 (124%) ለማሳካት ተችሏል።
- በዚህ ሩብ ዓመት ወደ ውጭ በሚላኩ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች ላይ 99% ተቀባይነት ያለው እና የተቀባይ ሀገር ቅሬታን (Notification) ለመቀነስ ታቅዶ 97 % ተቀባይነት ያገኘ ምርት መላክ ተችላል:
- በዚህ ሩብ ዓመት 28 የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎችን ላይ የመስክ ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ 23 (82%) ላይ ሞያዊ ድጋፍ መስጠት ተችሏል:
- በዚህ ሩብ ዓመት የሮዝ ምርት ወደ አውሮፓ ህብረት ልከው FCM ተባይ የተገኘባቸው እና ለNPPO በተላከው መረጃ መሰረት 5 የሮዝ ምርት ላኪዎች ወይንም እርሻዎች ላይ የኦዲቲንግ ስራ ተሰርቷል::
- በዚህ ሩብ ዓመት የ2024 አገራችን 'Xyllella Fastidosa' ከሚባል በሽታ ነጻ መሆንዋ 'Detection Survey and Diagnostic PCR test' እንዲሰራ በማድረግ በሽታው በሀገራችን አለመኖሩ ለአውሮፓ ህብረት ሪፖርት ተልኳል።
- ለዕፅዋትና ዕፅዋት ዉጤቶች ተቀባይ ሀገር የተባይ ስጋት ትንተና ቴክኒካል መረጃ/ሰነድ የመላክ ስራ በዚህ ሩብ ዓመት በቁጥር 4 ታቅዶ 3 መረጃ በማሰባሰብ ለሚመለከተው አካል ተለኳል::

- የሰሊጥ አምራቾች በሳልሞኔላ ምክንያት ወደ አውሮፓ ኤክስፖርት መቀዛቀዝ እንዳይከሰት ተገቢ የሆነ የላብራቶሪ ምርመራ እንዲያካሂዱ መከታተል ተደርጎል፡፡

በFalse Codling Moth/FCM/ ተባይ ዙሪያ: -

- ተባዩን ለመቆጣጠር የተሰሩ ስራዎች ዝርዝር 'Rapid Assessment of FCM in Cut Flowers of Roses in Ethiopia' የአዉሮፓ ህብረት ተቆጣጣሪ ድርጅት እንዲያዉቀዉ ለDG SANTE ሪፖርት ተልኳል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት ወደ አውሮፓ ህብረት ለሚልኩ የሮዝ የአበባ ምርቶች በኤርፖርት ጣቢያ መውጫ በር በኩል የFCM እና ሌሎች ተባዮችን ኢንስፔክሽን ስራ ተሰርቷል፡፡
- የአውሮፓ ህብረት FCMን የመቆጣጠር "Systems Approach" እንድንጠቀም በተጠቆመዉ መሰረት 'Systems Approach for FCM Risk Management on Rose Plants in Ethiopia' በ'CBI Ethiopia' በጀት ድጋፍ የባለስልጣኑ ባለሙያዎች ፣ ባለድርሻ አካላት፣ የአበባ እርሻ ባለሙያዎች እና የኔዘርላንድ ከፍተኛ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ሰነዱ የተዘጋጀ ሲሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ቫሊዴት/Validate/ ተደርጎ ለአውሮፓ ህብረቱ ተልኳል::
- በዚህ ሩብ ዓመት የሮዝ ምርት ወደ አውሮፓ ህብረት የሚልኩ እርሻዎችን 'Registration ID' እና የማምረቻ ኮድ /Production Code/ ስራ እየተጠናቀቀ ሲሆን ሲጠናቀቅ ለአውሮፓ ህብረት ይላካል፡፡
- የ'Pelargonium' ቁርጥራጭ ወይንም ምርት ወደ አሜሪካ ሀገር ለሚልኩ ለሁለት እረሻዎች ተፈላጊውን የመስክ ክትትል በማድረግ እና ተፈላጊውን የእርሻዎች የተባይ መከላከያ ዘዴዎች መረጃዎችን በመፈተሽ ለአሜሪካ 'NPPO' ሪፖርት ተልኳል::

**ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፀዋት እና የዕፀዋት ዉጤቶች**

- ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ዉጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች ላይ በዚህ 6 ወር 30,000 ቶን የኢንስፔክሽን ሥራ ለመስራት ታቅዶ ክንውን 55266 ቶን (>100 %) የኢንስፔክሽን ሥራ በማከናወን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የተደረጓል፡፡ ለአፈጻጸም ከፍተኛ መሆን በልዩ ፈቃድ ለቢራ ፋብሪካ የገባው የገብስ ምርት መጠን ከፍተኛ መሆኑ እንዲሁም ቀደም ብሎ በአዳማ በኩል ፍራንኮቫሉታ ተጠቃሚ ሆነናል በሚል የግንዛቤ ክፍተት የጉምሩክ ጽ/ቤት መልቀቂያ ሳይጠይቅ ምርቶችን እንዲገቡ ሲያደርግ የነበረዉ ክፍተት እንዲታረም በመደረጉ ሁሉም የፍራንኮቫሎታ ተጠቃሚ አስመጪዎች ያለ መልቀቂያ ፈቃድ እንዳይገቡ በመከልከላቸዉና ሁሉም መልቀቂያ ፈቃድ ወስደዉ ምርቶች መግባት በመጀመራቸዉ የመጣ ከፍተኛ ሪከርድ ነዉ::

በዝርዝር ሲታይ

- ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች የሚገቡባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ የጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ በዚህ ሩብ ዓመት በቁጥር 1,012 ለመስጠት ታቅዶ ክንውን 707 (70%) መስጠት ተችሏል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት በድህረ መግባት ኳራንቲን (Post Entry Quarantine) ኳራንቲን ለሚያስፈልጋቸው ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች ክትትል እናምርመራ ለማድረግ 3 ታቅዶ በተባይ ቅኝትና አሰሳ ዴስክ በ3 ምርቶች (100 %) በድህረ መግባት ኳራንቲን እንዲያልፉ የማስገቢያ ፈቃድ ተሰቷል::
- በገቢ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶች፣ ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶችና ሌሎች የግብርና ግብዓቶች ላይ የመግቢያ መስፈርቶችን አሟልተው እንዲገቡ በዚህ ሩብ ዓመት በቁጥር 1088 በዕቅድ ተይዞ 964 (89%) የቅድመ ማስገቢያ ፍቃድ ተሰጥቷል፡፡
- ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤቶች ላይ የተባይ ስጋት ትንተና የመስክ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ 2 ታቅዶ 2 (100%) (በማንጎ እና በስትሮበሪ) ከባለድረሻ አካላት ጋር በመሆን መረጃ ተሰብስቧል::
- አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን ለማስፋት ወቅታዊ ዓለም አቀፍ የምግብ ደህንነት ስታንዳርዶችን እና የተመረጡ ሃገራትን የማስገቢያ መስፈርቶች (ሰነዶችን) መገምገምና መሰል ስራዎች ከናሽናል ኮዴክ ኮሚቴ ጋር በመሆን የአንድ አመት የትግበራ እቅድ በማዘጋጀት ለመስራት ሁኔታዎች የተመቻቹ ሲሆን የሃገር ውስጥ የመሰረታዊ እርሻ ምርቶችን ስታንዳርድ ዝግጅትና ክለሳ ለማድረግም ከኢትዮጵያ ስታንዳርድ ኢንስቲቲዩት ጋር ምክክር ተደርጓል፡፡

**የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች**

- በዚህ 6 ወር በገቢና ወጭ የግብርና ምርቶች ላይ የብቃት ማረጋጋጫ ለሚጠይቁ ተገልጋዮች የባለሙያ፣ የቢሮ፣ የመጋዘን ኢንስፔክሽን በማካሄድ እና ሌሎች መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸው በማረጋገጥ በቁጥር 570 ለመስጠት ታቅዶ 387 (68%) የብቃት ማረጋገጫ መስጠት ተችሏል፡፡

## 2.3 የእፀዋት ዝርያ ጥበቃና ዘር ጥራት ቁጥጥር

- ለ15 አዲስ በዘር ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅደ ለ19 አዲስ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠ ሲሆን በተጨማሪ ለ19 ነባር ድርጅቶች እድሳት በመደረጉ በድምሩ 34 የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው ከፍ ያለበት ምክንያትም ወደ ዘፍ ሥራ አዲዲስ ተቋማት በመምጣታቸው ነው፡፡

- ለ80 በምርምር የቀረቡ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎችን ግምገማ ለማካሄድ ታቅዶ 85 እጩ ዝርያዎች ቀርበው የተገመገሙ ሲሆን አፈጻጸሙም 100+% ነው አፈጻጸመሙ ከዕቅዱ በመጠኑም ቢሆን ከፍ ያለው በክልል የሚገኙ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከአቅራቢያ የምርምር ተቋማት ገምጋሚ ባለሙያዎችን በመጠቀም ስራው እንዲከናወን በመደረጉ ነው፡፡
- በቁጥር 120 ከውጪ የገባ ዘር ናሙና ጥራቱ በላብራቶሪ እንዲፈተሽ ለማድረግ ታቅደ 166 የተከናውነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ የሆነ ሲሆን ከፍ ያለበትም ምክንያት አስመጪዎች ዶላር በማግኘታቸው ማስመጣት በመቻላቸው ነው፡፡
- 244,608 ኪሎግራም ከውጭ አገር ሚገባ ዘር በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 146,759 ኪሎ ግራም በቁጥጥር ስር ያለፈ ሲሆን አፈጻጸሙም 60% ነው አፈጻጸሙም ዝቅ ያለት ምክንያት የናሙናዎቹ ወካይ መጠን ወይም lot size አነስተኛ ስለነበረ ነው ::

**የዕጽዋት ምርትና ግብዓት ላቦራቶሪ**

- በዓመቱ 250 እንዲሁም በመጀመሪያው ሩብ አመት በ50 የተለያዩ የአትክልትና የሰብል ዘር ናሙናዎች ላይ የላብራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ ለማከናወን እና ውጤት ለማሳወቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ለጥራት ፍተሻ ላቦራቶሪው የቀረበው የናሙና ብዛት መጠን ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በሩብ ዓመቱ በ108 የተለያዩ የአትክልት/የሰብል ናሙናዎች ላይ የጥራት ፍተሻ ስራ ተከናውኗል፡፡ ይህም አፈጻጸም በመቶኛ 216% ነው፡፡
- እንዲሁም በሁለተኛው ሩብ አመት በ70 በተለያዩ የአትክልትና የሰብል ዘር ናሙናዎች ላይ የላብራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ ለማከናወን እና ውጤት ለማሳወቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን በሁለተኛው ሩብ ዓመት ለጥራት ፍተሻ ላቦራቶሪው የቀረበው የናሙና ብዛት በመጠን ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በሩብ ዓመቱ በ98 የተለያዩ የአትክልት/የሰብል ናሙናዎች ላይ የጥራት ፍተሻ ስራ ተከናውኗል፡፡ ይህም አፈጻጸም በመቶኛ 140% ነው፡፡
- በዚህ 6ወር ዉስጥ በ120 በተለያዩ የአትክልትና የሰብል ዘር ናሙናዎች ላይ የዘር ጥራት ፍተሻ ለማከናወን እና ውጤት ለማሳወቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን በስድስት ወሩ ውስጥ ለጥራት ፍተሻ ላቦራቶሪው የቀረበው የናሙና ብዛት በመጠን ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በስድስቱ ወር በ206 የተለያዩ የአትክልት/የሰብል ናሙናዎች ላይ የጥራት ፍተሻ ስራ ተከናውኗል፡፡ ይህም አፈጻጸም በመቶኛ 171.66% ነው፡፡
- በዚህ 6ወር ዉስጥ ከክልል በሚመጡ በ20 የተለያዩ የሰብል/የአትክልት ዱፐሊኬት (Duplicate) ናሙናዎች ላይ የንጽጽር የላብራቶሪ ፍተሻ ስራዎች ለማከናወን ታቀዶ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን ለጥራት ፍተሻ ላቦራሪው መምጣት የቻለው የናሙና መጠን

አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በሩብ ዓመቱ በ18 ናሙናዎች ላይ ብቻ የንጽጽር የላብራቶሪ ፍተሻ ተከናውኗል፡፡ ይህም አፈጻጸም በመቶኛ 90% ነው፡፡

## 3. የእንስሳት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር

### 3.1.የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

**ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እንዲላክ የኢንስፔክሽ አገልግሎት መስጠት፣**

- የቅድመ ዕርድና ድህረ እርድ ምርመራ በማከናወን እና የቄራዎችን ሀይጅንና ሳኒቴሽን እንዲጠበቅ በመቆጣጠር ጤንነቱ ፣ ደህንነቱና ጥራቱን የጠበቀ ለወጭ ገበያ የሚቀርብ እና ለሰው ምግብነት የሚውል የስጋ ምርት እንድመረት በማስቻል ኣእንዲሁም በላቦራቶሪ ምርመራ የስጋ ደህንነት እንዲረጋገጥ በማድረግ 7,500 ቶን ሥጋ እና ተረፈ ስጋ ምርት ወደውጭ እንዲላክ ታቅዶ በድምሩ 9512.4 ስጋ እና ተረፈ ስጋ ተልኳል ይህም የእቅዱን 126.8% ነው፡፡

**በግመሽ ዓመቱ ደህንነቱና ጥራቱ ተረጋግጦ ወደ ተቀባይ አገራት ለሚላክ ስጋና ተረፈ ስጋ የተሰጠ የደህንነትና ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት**

**ዓለም አቀፍ የሥጋ ደህንነት እና ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የስጋ ምርት ወደ ውጪ እንዲላክ ማድረግ፡፡**

- ለምርቶቹ የተሰጠ የደህንነትና ጤንነት ማረጋገጫ ሰረተፊኬት 3000 በግማሽ በአመቱ ታቅዶ 4211 ተሰጥቷል አፈጻጸሙ 140% ነው፡፡

**በእንስሳት ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን**

- በ14 ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ በ14 ተቃማት ላይ ተከናውኗል፡፡አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡ባለፉት ስድስት ወራት ለ28 ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ በ28 ተቋማት ላይ ተከናውኗል፡፡

**ጥራቱና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ የተረጋገጠ የእንስሳት ምርት ናሙናዎች**

- በዚህ 2ኛ ሩብ አመት 180 የእንስሳት ምርት ናሙናዎች ላይ የፊዚኮ-ኬሚካል እና የማይክሮባዮሎጂ ጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ሥራዎች ለማከናወን ታቅዶ ከተለያዩ አከባቢዎች በተሰበሰቡ 260 የሥጋ እና የወተት ምርት ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት

ምርመራ ሥራ የተከናወነ ሲሆን እስከዚህ ሩብ አመት 300 ታቅዶ 411 (>100%) ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ፍተሻ ማካሄድ ተችሏል። ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

- የሥጋ ምርት ናሙናዎችን ከዱከም፣ ቢሾፍቱ እና ሞጆ ከተሞች ከሚገኙ 7 ኤክስፖርት ቄራዎችና አንድ የእንስሳት ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅት ናሙናዎችን በመሰብሳብ የመድሃኒት ቅሪትና የማይክሮባዮሎጂ ጥራት ምርመራ የተከነወነ ሲሆን የወተት ምርት ናሙናዎችን ደግሞ ከ7 ከተሞች (አዲስ አበባ፣ ሰበታ፣ ጫንጮ፣ ኩዩ፣ ፍቼ፣ ሆለታ እና ለጋ-ጣፎ) በተሰበሰበው የጥሬ ወተት የምግብ ንጥረ ነገር ይዘት፣ የአፍላቶክሲን እና የማይክሮባዮሎጂ ጥራት ምርመራ ለመሥራት ተችሏል።

**ለኮመርሻል የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ**

- ባለፉት ስድስት ወራት ለ35 **የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ** ለመስጠት ታቅዶ ለ25 **የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች** የድጋፍና ክትትል ሰራዎችን በማከናወን ለመደገፍ ተችሏል አፈጻጸሙም 71.43% ነው።

**በግማሽ ዓመቱ የኦድት ምርመራ የዓለም አቀፍ የምግብ ደህንነት ስርዓት (ISO 22000) /HACCP መስፈርት አሟልተው የተገኙ ኤክስፖርት ቄራዎች**

- በ11 ኤክስፖርት ቄራዎች የስጋ ምርት ተቀባይ አገራትን እና ዓለም ዓቀፍ የምግብ ደህንነት ስርዓት መስፈርቶችን አሟልተው የሚሰሩ መሆናቸውን 2 ኦዲት በማድረግ የምግብ ደህንነት የአሰራር ስርዓቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ታቅዶ 2 ተከናውኗል። በተገኘው ግብረመልስ መነሻነትም 3 ቄራዎች በኦዲት ግኝታቸው ላይ በ1ወር እራሳቸውን እንዲያስተካክሉ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል ።
- በ UNIDO ፕሮጀክት ድጋፍ 2 ቄራ በቻይና ሬጉላቶሪ አካል ግምገማ ተደርጎበታል ፤- የቻይና ኢንፖርት ኤክስፖርት አሶሴሽን ወደ ሀገራችን መጥተው በየምግብ ማቀነባበሪያ ተቋማት መሰረተ ልማት፤ፋሲሊቲ ላይ ጉብኝት አድርገዋል። በተጨማሪም ወደ ቻይና ገበያ ለመግባት GACC questionnaire ተሞልቶ ወደ ግብርና ሚኒስቴር ተልኳል።
- የስጋ ሴክተሩን ዲጅታላዝ ለማድረግ ሲስተሙ አልቆ ለባለሞያዎች በሰርቪስ ዲጅታላይዜሽን፤ኢ-ለርኒግ እና ዌብሳይት ስልጠና ተሰጥቷል።
- በእንሰሳት ጤና እና ደህንነት አዋጅ ላይ የኢትዮጲያ ግብርና ባለስልጣን አሁን ባለው አደረጃጀት መሰረት እንዲታኝ ስራዎች ተሰርተዋል።

## 3.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ ወደ ውጭ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች

- ባለፉት ስድስት ወራት 195000 ወደ ውጭ የሚላክ የቁም እንሰሳት/ዳልጋ ከብት፣ ግመል/ በግ፤ፍየል/ በኳራንትን ጣቢያዎች ውስጥ በማቆየት አስፈላጊን ክትባትና የጤና

ምርመራ በማድና ጥራቱና ጤንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 280000 የቁም እንስሳት ጥራትና ጤንነቱን በማረጋገጥ ወደ ተቀባይ ሀገራት የተላከ ሲ"ሀን አፈጻጸሙም 107% ሆኗል፡፡

- ባለፉት ስድስት ወራት 272000 ወደ ውጭ የሚላክ የለማ እንቁላል ጤንነቱ እና ደህንነቱ በማረጋገጥ ወደ ውጭ ለመለላክ ታቅዶ 3420000የለማ እንቁላይ በኳራንቲን ሰርትፊኬሽን በመስጠት እንዲወጣ የተረገ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡
- ባለፉት ስድስት ወራት ወደ ተቀባይ ሀገራት የማርና ሰም ምርት ለሚል ድርጅቶች የኢንስፔክሽን እንዲሁም የላብራቶሪ ምርመራ ተደርጐላቸው 220 ቶን ማርና ሰም ለመላክ ታቅዶ 118 ቶን የጤና አገልግሎት ሰርትፊ"ከሽን በመስጠት እንዲላኩ የተደረገ ሲሆን ይም አፈጻጸሙ 56% የሆነ ሲሆን አፈጻጸሙም ዝቅ ያለበት ምክንያት የሀገር ውስጥ ፍላጐት መጨመር እና የዋጋ ንረት መኖሩ ነው፡
- በባለፉት ስድስት ወራት 1785450 ያለቀለት ቆዳና ሌጦ የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ 2913765 የሳኒተሪ ሰርትፊኬት በመስጠት ከሀገር እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙም >100% ሆኗል፡፡
- ባለፉት ስድስት ወራት ለ345000 ወደ ሀገር የሚገባ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል ጤንነቱ እና ደህንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 251810 /73%ተከናውኗል፡፡
- ባለፉት ስድስት ወራት ለ 138 ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባ የተሸሸለ ዳልጋ ከብት ጤንነቱ እና ደህንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 298 /ከ100% በላይ ተከናውኗል፡፡
- ባለፉት ስድስት ወራት 6000 ወደ ዐገር ለሚገባ አባላዘር ጤንነቱ እና ደህንነቱ የማረጋገጥ ሥራ ለመስራት ታቅዶ 96955 ከ100% በላይ ተከናውኗል፡፡

## 3.3 የእንስሳት መድሃኒት ጥራት ደህነነትና ፈዋሽነነት ማረጋገጥ

### ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት

- በ2017 በጀት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት 1425 ቶን ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ታቅዶ 1854 ቶን የእንስሳት መድኃኒት ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም >100% ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ተገልጋዮች አገልግሎቱን ፈልገው በብዛት ባመምጣታቸው ነው፡፡
- 2017 በጀት ዓመት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት ተገምግሞ፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ 37 የእንስሳት መድሃኒት ለመመዝገብ ታቅዶ 104 የእንስሳት

መድኃኒት እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም >100% ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት መስፈርቶቹን ያሟሉ መድሃኒቶች በብዛት በመኖራቸው ነው፡፡

**የመድሃኒት ናሙዎችን ላይ የተካሄደ የጥራት፣ ደህንነት እና ፈዋሽነት የላቦራቶሪ ምርመራ**

- በዚህ 2ኛ ሩብ አመት 75 የመድኃኒት ምርት ናሙናዎች ላይ የፊዚኮ-ኬሚካል ጥራት ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 113 ናሙናዎች ላይ ምርመራ ማካሄድ ተችሏል፡፡ እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት ከተገልጋዮች በሚቀርቡ 150 የመድኃኒት ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በ188 (>100%) ናሙናዎች ላይ የጥራት ምርመራ ሥራዎችን ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በግማሽ አመት የላቦራቶሪ ምርመራ ከተሰራላቸው 188 የመድኃኒት ናሙናዎች ውስጥ 13 (6.9%) ተፈላጊውን የፊዚኮ-ኬሚካል ጥራት መስፈርት ያላሟሉ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት**

- በ2017 በጀት ዓመት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት ለ187 የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንሰጣለን እናድሳለን ብለን አቅደን 202 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰቷል፡፡ አፈጻጸሙም >100% ሆኗል፡፡

**የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን**

- በ2017 በጀት ዓመት እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት 314 የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን እናረጋለን ብለን አቅደን 239 የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን አካሂደናል፡፡ አፈጻጸሙም 76% ሆኗል፡፡

**በኢንስፔክሽን ወቅትም የታዩት ክፍተቶች እና የተወሰዱ እርምጃዎች፡-**

- አንድ አስመጪ የመጠቀሚያ ጊዜ አልፎባቸው የተከማቹ 428 ብልቃጥ ሆርሞን እንዲወገድ አድርገናል፡፡፡፡ ለተወገዱ መድሃኒቶችም ለሚመለከተው ክፍልም ማረጋገጫ ተጽፏል፡፡
- በመግቢያና መውጫ ኬላ ላይ የጥራት ደረጃቸውን ለማረጋገጥ ለተወሰደ ናሙና ከደረጃ በታች በመሆኑ 30¸000 ብልቃጥ አይቨርመክቲን የሚባል የእንስሳት መድኃኒት እንዲወገድ አድርገናል፡፡ ለተወገዱ መድሃኒቶችም ለሚመለከተው ክፍልም ማረጋገጫ ተጽፏል፡፡
- 2 ባች በተለያየ ጊዜ ወደ ሃገር ሊገቡ የነበሩ የእንስሳት መድኃኒቶች የመግለጫ ጽሁፍ (labeling) ችግር ስለነበረበት ከኬላ እንዳይለቀቅ ተደርጉል፡
- የአራት መድሃኒቶች 15 ባች የላቦራቶሪ ውጤት ከደረጃ በታች በመሆኑ ምዝገባው እንዲቋረጥ እና ድርጅቱ በደብዳቤ እንዲያውቀው ተደርጉል፡፡

- ከምዕራብ ጉጂ ዞን በሁለት ወረዳዎች ማለትም ደሩ ደሊፊኖ እና ጨሜ ቂራ በተከሰተ የ23 ግመሎች ሞት በደረሰን ጥቆማ መሠረት የባለሥልጣኑ ባለሙያዎች በቦታዉ በመገኘት፤ የተከሰተውን የመድኃኒት ጎጂ ባህሪያት መንስኤ ለማጣራት የክትባት ናሙና በ AUPANVAC ላብራቶሪ የተመረመረ ሲሆን በውጤቱ መሰረት ክትባቱ የጥራት ወይም የደህንነት ችግር የሌለው መሆኑን በማረጋጋጥ መንስዔው ምን እንደሆነ ሌላ ጥናት እንዲደረግበት በደብዳቤ እንዲያውቁት አድርገናል።
- ከሌላ አምራች ድርጅቶች በደረሰን ጥቆማ መሰረት የአንድ አምራች ድርጅት የመድኃኒቶቹን ጥራት በመቀነስ የሚሸጥበትን ዋጋ ይቀንሳሉ ምርታቸው ከአንድ አመት በኋላ ጥራቱ እንደሚጓደል መረጃ በደረሰን መሰረት በእንስሳት መድኃኒት አምራች ድርጅቱ ከአመት በፊት የገቡ እና retain የተደረጉ ናሙናዎች ጥራት ተረጋግጦ እንዲላክልን ላቦራቶሪ ልክን ያሰራን ሲሆን በውጤቱ መሰረት መድሃኒቱ የጥራት ወይም የደህንነት ችግር የሌለውና ጥቆማው መሰረተ ቢስ መሆኑን ማረጋጋጥ ተችሏል።

## 3.4 ጥራትና ደህነነቱ የተረጋገጠ የእንሰሳት መኖ

## የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ መኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት

- ባለፉት ስድስት ወራት በአጠቃላይ ለ352 የመኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ 284 ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 81% ነው።የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስን ያካተተ ሲሆን 56 የመኖ ንግድ ተቋማትና በተቋማቱ የሚሰሩ ባለሙያዎች ለዕድሳት አገልግሎት ባለመቅረባቸው የተቋማት እና የሙያተኞች ዕድሳት አገልግሎት አፈጻጸሙ በመጠኑ ዝቅ ሊያደርገው ችሏል። በአሰራር መመሪያው መሰረት በቀጣይ ሩብ ዓመት በቅጣት ሊታደስ ይችላል።

**ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ መኖ እና የመኖ ግብዓት**

- ባለፉት ስድስት ወራት በአጠቃላይ 2750 ቶን መኖና የመኖ ግብዓት **ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ 5184.15 ቶን ማከናወን በመቻሉ** አፈጻጸሙ 100+% ሆኗል።አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነው የቀረበው የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ጥያቄ ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑና አዳዲስ አስመጪዎች ወደ ስራው በመግባታቸው ነው።

**የመኖ እና የመኖ ጥሬ ግብዓት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የጥራት እና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ**

- ለ35 የመኖ ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ በ 38 ናሙናዎች ላይ ምርመራ ማካሄድ የተቻለ ሲሆን እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት 65 ታቅዶ 68 (>100%) የመኖ ናሙናዎች ላይ ምርመራ ማካሄድ ተችሏል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡
- የመኖ አፍላቶክሲን ምርመራ ከተሰራላቸው 68 ናሙናዎች ውስጥ 40 (58.8%) ከሚፈለገው ስታንደርድ መጠን በላይ እንዲሁም የማይክሮባዮሊጂ ጥራትና ደህንነት ምርመራ ከተሰራላቸው 33 ናሙናዎች ውስጥ 14 (42.43%) የባካይ ተዋሲያን መጠን ከሚፈለገው ስታንደርድ በላይ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- የመርዛማ ሚኔራል (ሊዲ እና ካዲሚየም) የተሰራላቸው 38 ናሙናዎች ሁሉም ተፈላጊውን ቅበላ መስፈርት የሚያሟሉ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- በተጨማሪም በመኖ ሬጉላቶሪ ሥራ ክፍል ለምርምር አለማ በተሰበሰበው 224 የዶሮ መኖ ናሙናዎችን ላይ የመኖ ንጥረ ነገር ይዘት/ጥራት ምርመራ ከተሰራላቸው ውስጥ በፕሮቲን 36 (16%) እና በፋይበር 56 (25%) ይዘታቸው ከስታንዳርድ በታች መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ የተመረተ የተቀነባበረ መኖ እና የመኖ ግብዓት**

- ባለፉት ስድስት ወራት በአጠቃላይ 85227 ቶን መኖና የመኖ ግብዓት **ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ እንዲቀነባበር ወይም እንዲመረት ለማድረግ ታቅዶ 149917 ቶን ማከናወን በመቻሉ** አፈጻጸሙ 100+% ሆኗል፡፡አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነው መረጃው የተሰወሰደው ብቃት ማረጋገጫ ካላቸው 30 የመኖ ማቀነባሪያዎች በመሆኑ ነው፡፡

**በእንስሳት መኖ እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን**

- በ 29 የእንስሳት መኖ አምራች ተቋማት ላይ የኢንስፔክሽን ስራ ለማከናወን ታቅዶ በ20 የመኖ ንግድ ተቋማት የተከናወነ ሲሆን፣ አፈጻጸሙ 68.96% ሆኗል፡፡ እስከዚህ ሩብ ዓመት 155 ታቅዶ 138 ሲከናወን አፈጻጸሙ 89% ሆኗል፡፡የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ዝቅተኛ የሆነው በአማራ ክልል በሚገኙ 51 የመኖ ንግድ ተቋማት የኢንስፔክሽን ሥራ ባለመከናወኑ ነው፡፡

**<u>በቅድመ እና ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ግኝት ላይ የተወሰደ እርምጃ፡-</u>**

- ለ3 የእንስሳት መኖ አምራች ድርጅቶች የመኖ ላቦራቶሪ ውጤትንና በኢንስፔክሽን ወቅት የታዩባቸውን ጉድለቶች እንዲያስተካክሉ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

- ለ3 የእንስሳት መኖ አምራች ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እገዳ ደብዳቤ የተጻፈ ሲሆን ከ3ቱ ድርጅቶች አንዱ ደብዳቤው ከደረሰው በኋላ ጉድለቱን በማረሙ እገዳው እንዲነሳለት በጻፈው ደብዳቤ መሰረት፣ በኢንስፔክተሮች ተረጋግጦ እገዳው ተነስቶለታል፡፡
- 1 ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘትያቀረበው ሰነድ ከአሰራር መመሪያው አኳያ የማያሟላ በመሆኑ ውድቅ ተደርጓል፣
- 1 ተቋም በቅድመ ኢንስፔክሽን ምልከታ ወቅት መመሪያውን የማያሟላ በመሆኑ ውድቅ ተደርጎ፣ በድጋሚ ተቋሙ ጉድለቱን ማስተካከላሉን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ በመጻፉ ምክንያት፣ ተቋሙን ሁለተኛ ዙር የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈልና በድጋሚ በባለሙያዎች በተደረገ የቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡
- በመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች ተቋማት ላይ በኢንስፔክተሮች በተደረገው ቁጥጥር 5 የዘይት ፋብሪካዎች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲያወጡ ተደርጓል፣
- በጉለሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ መነን ፖሊስ ጣቢያ ከመኖ ጥራትና ደህንነት ጋር ተያይዞ ላቀረበው ጥያቄ ቅሬታ አቅራቢው ገዝቶ ለከብቶቻቸው ሳይመግቡት ከቀረ 7.5 ኩንታል መኖ ላይ ወካይ ናሙና በመውሰድ ናሙናውን ወደ ተቋማችን ላብራቶሪ በመላክ በላብራቶሪያችን የጥራትና ደህንነት ፍተሻ ተደርጎ የተገኘውን ውጤት የጠቅላላ አፍላቶክሲን እና የአፍላቶክሲን ቢ1 እንዲሁም ይስት ወይም ሞልድ መጠኑ የኢትዮያን የጥራት ደረጃ የማያሟላ መሆኑን ለጠያቂው ክፍል እንዲደርስ ተደርጓል፡፡
- የመኖ ማቀነባበር ብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው መኖ ያመርታል ተብሎ ለቀረበ አንድ ቅሬታ፣ የኢንስፔክሽን ቡድን ባደረገው ቁጥጥር፣ ተቋሙ የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት ጥያቄ ቢያቀርብም፣ ያቀረበው ሰነድ የተሟላ ባለመሆኑ ውድቅ ተደርጓል፡፡

## 3.5 ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት

- 2ኛ ሩብ አመት የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ ሥራዎችን በማጠናከር በ16 ዓይነት የላቦራቶሪ ምርመራ ዓይነቶች ላይ እውቅና ማግኘት የሚያስችል በርካታ ሥራዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡
- ለኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ ማረጋገጫ ሰነዶችንና መረጃዎችን አዘጋጅቶና አደራጅቶ ማቅረብ ተችሏል፤ የላቦራቶሪ ብቃት ግምገማ ወይም የውጭ ኦዲት ሥራዎች በእውቅና ሰጪ ተቋም እንዲካሄድ ተደርጓል፤ ማዕከሉ

የላቦራቶሪ ኦዲት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ ወይም የእርምት ሥራዎችን በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ አጠናቆ ሪፖርት በማድረግ የኢትዮጵያ አክሪድቴሽን አገልግሎት ጽ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

- በዚህ 2ኛ ሩብ ዓመት 20 ነባርና አዳዲስ ስታንዳርድ የአሰራር ፕሮሲጀሮችን እና የላቦራቶሪ ምርመራ ሥነ-ዘዴዎችን ለማዘጋጀት፣ ለመከለስ እና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ታቅዶ 38 (>100%) እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት 84 ታቅዶ 97 የተለያዩ የአሰራር ፕሮሲጀሮችን፣ የምርመራ ሥነ-ዘዴዎችን እና ማኑዋሎችን በመከለስና በማዘጋጀት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡
- እስከዚህ 2ኛው ሩብ ዓመት 8 የተለያዩ የላቦራቶሪ ምርመራ ስነ-ዘዴዎች ትክክለኛነት ማረጋገጫ (ትስት ሜተድ ቫሊዴሽን እና ቬሪፊኬሽን) ሥራዎችን ለማከወን ዕቅድ ተይዘው 4 ማከናውን ተችሏል፡፡
- በዚህ 2ኛ ሩብ አመት የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ጥገና፣ ካሊብሬሽን እና ኮምፕሊያስ ቨርፊኬሽን ለማሰራት የተያዘው ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል 22 የተለያዩ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች የመለየት፣ የጥገና እና ካሊብሬሽን አገልግሎት ግዥ ዝርዝር መግለጫ ፍላጎት በማዘጋጀት ለግብርና ሚ/ር ድራይቭ ፕሮጄክት የበጀት ድጋፍ ፕሮፖዛል የማቅረብ ሥራ ተሰርቷል፤ የአገልግሎት ግዥ ጨረታ የማውጣት ሥራ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡
- እስከዚህ 2ኛ ሩብ አመት የላቦራቶሪ ምርመራ ብቃት ማረጋገጫ (Proficiency Testing, PT) ናሙናዎችን አለም አቀፍ እውቅና (ISO 17034 certified PT sample providers) ካላቸው ድርጅቶች በማስመጣት 6 የምርመራ ብቃት ማረጋገጫ ሥራዎች ላይ ለመሳተፍ እቅድ የተያዘ ሲሆን አሜሪካ፣ ኢጣሊያን፣ ኢንግሊዝ እና ደቡብ አፍርካ ከሚገኙ የላቦራቶሪ ምርመራ ብቃት ማረጋገጫ ናሙና አቅራቢ ድርጅቶች ጋር በመጻጻፍ እንዲሁም ከዓለም አቀፍ የአቶሚክ ኃይል ኤጀንሲ ጋር ድጋፍ ሊያስገኙ የሚችሉ የሥራ ግንኙነት በመፍጠርና 9 (>100%) የላቦራቶሪ ምርመራ ብቃት ማረጋገጫ ሥራዎች ማከናወን ተችሏል፡፡

## 4. የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር

### 4.1 በስልጠና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር

የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር

- በሜካናይዜሽን አገልግሎት አሰጣጥና የቢዝነስ ፕላን ዝግጅት ላይ አንድ ሰው እንዲሰለጥን ተደርጓል፡፡
- የስራ ዘርፉ አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ የሚሆኑበትን አሰራር ለመዘርጋት ሁለት ሰዎች በኢ-ሰርቪስ ላይ እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡

- በሀገር ደረጃ የተፈጠረውን መልካም ዕድል በመጠቀም በኢ-ኮዲንግ ስልጠና በመሳተፍ ሁለቱም የክፍሉ ሰራተኞች ሰርቲፊኬት አግኝተዋል፡፡
- ሁለት የመኖ ሰራተኞች (የዴስክ ሃላፊ እና ባለሙያ) አጭር የውጪ ስልጠና እንዲያኝ ተደርጓል::
- በአደጋ ስጋት ልየታና ትንተና 14 የመኖ ፈጻሚ ባለሙያች ስልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ፣ /ISO 31000፡2018/፣ 100% ተከናውኗል፡፡
- ሁለት ሰርተፍኬሽን እስኪሞች ከኢትዮጵያ የደረጃዎች ኢኒስቲትዩት ጋር በመሆን ተዘጋጅተዋል ማለትም "FORTIFIED EDIBLE OIL CERTIFICATION SCHEME እና Certification scheme for beer' በሚል እርሶችኢኒስቲትዩት ጋር በመሆን ተዘጋጅተዋል፡፡
- ለሁለተኛ ዙር ለFSRP TOR በ"Support Development and Popularization of new Food Safety and Quality Standards" በሚል እርስ ተዘጋጅቷል፡፡
- የኢትዮጵያ ደረጃ እንዲዘጋጅላቸው ጥያቄ የቀረበባቸውን አዲስ የአፈር ማዳበሪያዎች የደረጃ ዝግጅት የሚረዳ ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ባለሙያዎችን በማሳተፍ ወርክ ሾፕ የተካሄደ ሲሆን ይህም ለደረጃ ዝግጅት ስራው የሚያግዝ ግብዓት ማስገኘቱ ከደረጃዎች ኢንስቲትዩት በመሆን ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ የቴክኒካል ኮሚቴ አባላትን በማሳተፍ አዲስ ደረጃ የማውጣትና ክለሳ የተጠየቀባቸውን የመከለስ ስራ ተሰርቷል፡፡
- National food safety and quality management control workshop' በሚል ከ 9 ክልሎች እና 11 የተለያዩ የምግብ ደህንነት እና ጥራትን ከሚመለከታቸው የመንግስት እና የግል ባለድርሻ አካላት ጋር በአዳማ ከተማ የምክክር መድርክ ተካሄዱል፡፡
- አጋር ድርጅት በሆነዉ COLEAD የተዘጋጀዉን ሁለት online ስልጠናዎች 'Risk Categorization for Inspection and Internal Audit' የተለያዩ ባለሙያዎች እንዲሰለጥኑ ተደርጓል::
- የኳራንታይን ጣቢያ ባለሙያዎች' ዴስክ ሃላፊዎች እንዲሁም የዋናው መ/ቤት በዕፅዋት ካራንታይንና ሬጉላቶሪ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ስር ያሉ ባለሙያዎች እና የዴስክ ሃላፊዎች እንዲሁም አጠቃላይ በሁለተኛዉ ዙር 19 ሰልጣኞች በትሬድ ማርግ ድርጅት ድጋፍ 'FCM, Servilance, and IPPC Regulation ርዕሶች ላይ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡
- ሁለተኛ ዙር ስልጠና (ከታህሳስ 4/2017 እስከ 6/2017) በትሬድ ማርግ ድርጅት/TMA በጀት ድጋፍ ፤ ለሰራ ክፍሉ ባለሙያዎች ፣ የጣቢያ ባለሙያዎች ፣ ለአበባ እርሻ

ባለሙያዎች እና ሆርቲካልቸር ማህበር ባለሙያዎች በአጠቃላይ ለ 21 ተሳታዎች በሰድስት የስልጠና ርዕሶች ስልጠና መስጠት ተችሏል::

- በተመረጡ 3 የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አገልግሎቶች ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የአፕልኬሽን ሶፍትዌር የበተፀገ ሲሆን በአጠቃቀሙ ላይ በ'Ehiopia Nwtherland Project' በጀት ድጋፍ ለ 12 ባለሙያዎች ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጎዋል::
- በግብርና ባለስልጣንና በአበባ አምራቾች ተባይ ቁጥጥር ስራዉን ለማየት የተገኙትን ክፍተቶች በስልጠና ለመሙላት ድጋፍ ለመስጠት በኔዘርላንድ ኢምባሲ በኩል በተመቻቸዉ መሰረት ከኔዘርላንድ በመስኩ ከፍተኛ ልምድና ስራ ላይ ያሉ ባለሙያዎች በግብርና ባለስልጣን ፤ በቦሌ አየር መንገድ ጣቢያ እና በኔዘርላንድ ኢምባሲ ከአምራችና ላኪ ድርጅቶች ጋር በመገናኘት ስራዉን የገመገሙ ሲሆን ዉይይቶችና ስልጠናም ተሰጥቷል።
- Technical Assistance On Delivery And Oversight of SPS Measures and Standards in Ethiopia Inception Report በበይነ መረብ ክትትል ተደርጎ ግብዓት ተሰቷል::
- ለማዕከሉ ባለሙያዎች፣ ሰራተኞች እና አመራሮች በጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ፣ የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራት ምርመራ እና ተያያዥ ቴክኒካል ሥራዎች ላይ ሥልጠና ለመስጠት በታቀደው መሠረት በተለያዩ የሥልጠና ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ባለሙያዎች እና አመራሮችን አቅም የመገንባት ሥራዎች ተሰርቷል። ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።
- የሥራ ላይ ደህንነት አጠባበቅ ላይ ለ 78 (43 ወንድ እና 35 ሴት) አጠቃላይ ሠራተኞች፣የሚኒላብ ቴክኖሎጂን አጠቃቀም እና የመድኃኒት የፊዚኮ-ኬሚካል ጥራት ምርመራ ላይ ለ 19 (17 ወንድ እና 2 ሴት) ባለሙያዎች በአለም ምግብና እርሻ ድርጅት ድጋፍ፣
- የእንስሳት ምርት እና ግብዓት የፊዚኮ ኬሚካል ጥራት ምርመራ፣ የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት እና ተያያዥ የላቦራቶሪ ፋሲሊቲ ማኔጅመት የንድፈ ሃሳብ እና የተግባር ስልጠና ለ 19 ባለሙያዎች (19 ወንድ እና 6 ሴት) በግብርና ሚ/ር ድራይቭ ፕሮጀክት ድጋፍ፣
- በወተት ምርት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር እና ተያያዥ ርዕሰ-ጉዳዩች ላይ ለ 7 (4 ወንድ እና 3 ሴት)፣ ባለሙያዎች በደቡብ ኮሪያ ዓለም-አቀፍ የልማት ትብብር ኢጀንሲ ፕሮጀክት ድጋፍ፣

- በጸረ-ተህዋስያን መድኃኒት በጀርሞች መለመድ፣ በምግብ ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር እንዲሁም በመድሃኒት ጥራት ምርመራ እና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች አጠቃቀም ላይ 3 (2 ወንድ እና 1 ሴት) ባለሙያዎች በውጭ አገር (ዛምቢያ፣ በሞሮኮ እና በህንድ)፣
- የመንግስት ኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት ትግበራ ላይ የማዕከሉ የግዥ አጽዳቂ እና ግዥ 7 ባለሙያዎች (3 ወንድ እና 4 ሴት) የንድፈ ሀሳብ እና የተግባር ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡
- ከአዳሚ ቱሉ ፀረ-ተባይ አዘጋጅ ፋብሪካ በተገኘው ጥቆማ መሰረት ከኦሮሚያና ከአዲስ አበባ የቁጥጥር አካላት ጋር በመቀኛጀት የችግሩን ነባራዊ ሁኔታ በመፈተሽ የመፍትሄ ምክረ-ሀሳብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡
- ከፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ ጋር አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ያሉ የአከባቢ እና ጤና ስጋቶችን እንዲሁም የፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ ተቋማት ነባራዊ ሁኔታ እና ህጋዊነትን አስመልክቶ ከኦሮሚያ ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመቀናጀት ጥናት (Assesment) ተሰርቶ ሰነድ እየተዘገጀ ነዉ፡፡
- ከሁሉም ክልሎች እና የከተማ መስተዳድሮች የፀረ-ተባይ ተቆጣጣሪ ተወካዮች እንዲሁም ከፌዴራል ባለድርሻ አካላት ጋር የፀረ-ተባይ ቁጥጥርን በተመለከተ ስልጠና እና የጋራ ምክክር ተደርጓል፡፡
- ከአለም የምግብና የእርሻ ድርጅት ጋር በመተባበር በዘርፉ ያሉ ህግ ማቀፎች የፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ የህግ ማዕቀፎችን ጨምሮ ለባለሞያዎች ስልጠና በሁለት ዙር ተሰቷል፡፡
- ለኤክስፖርት ቄራ ሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች በስራ ቦታቸው ላይ በተግባር የስጋ ምርመራ ስልጠና በUNIDO ፕሮጀክት ለ61 ባለሞያ ተሠጥቷል፡፡

**ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ**

- የኢትዮጵያን ስጋ ወደ ቻይና ገበያ ለማስገባት እንዲቻል፣ በቅድመሁኔታ የቀረበውን የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝር፣ በUNIDO ፕሮጀክት ድጋፍ፣ ከሆሎታ እና ደበረዘይት ምርምር ጣቢያዎች በተወከሉ ከፍተኛ የእንስሳት የስነ ምግብ ተመራማሪዎች እና ከስራ ክፍሉ በተውጣጡ ባለሙያዎች ረቂቅ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝር ተዘጋጅቷል
- ረቂቅ ሰነዱ 5 ሴት እና 25 ወንድ በድምሩ 30 ከመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪዎችና መኖ አቀነባሪዎች የተወከሉ በተገኙበት ተጨማሪ የግብዓት ማሰባሰቢያና የማረጋገጫ መድረክ ተካሂዷል፡፡

- በዩኒዶ የበጀት ድጋፍ ለ14 የመኖ ሬጉላቶሪ ባለሙያዎች በ/ HACCP/ የአደጋ ትንተና ወሳኝ መቆጣጠሪያ ነጥብ ላይ ለ 5 ቀናት የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና እንዲያኙ ተደርጓል፡፡
- በዩኒዶ የበጀት ድጋፍ ለ3 የመግቢያና መውጫ የመኖ ኢንስፔክተሮች በ/ HACCP/ የአደጋ ትንተና ወሳኝ መቆጣጠሪያ ነጥብ ላይ ለ 5 ቀናት የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና እንዲያኙ ተደርጓል፡፡
- በዩኒዶ የበጀት ድጋፍ ለ9 የመኖ ማቀነባሪያ ፋብሪካዎች በ/ HACCP/ የአደጋ ትንተና ወሳኝ መቆጣጠሪያ ነጥብ ላይ ለ 5 ቀናት የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና እንዲያኙ ተደርጓል፡፡
- ለ SNV-Ethiopia ከመኖ-ምግብ ደህንነት አንጻር ለሚከናወኑ ሥራዎች concept note በማዘጋጀት፣ በረቂቁ ላይ ከድርጅቱ ምክትል ቴክኒካል ዳይሬክተር፣ ስትተራቴጂክ ም/ዳይክተር እና ከምግብ ደህንት ባለሙያ ጋር የጋራ ውይይት የተካሄደ ሲሆን፣ በመጪው የፈረንጆች አዲስ ዓመት በሰነዱ ላይ በመፈራረም ወደስራ ለመግባት የሚያስችል ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

- ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት እና የፕሮጀክት ጽ/ቤት አስተባበሪዎች፣ የልማት አጋር ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት እንዲፈጠር በማድረግ የተቋሙ ተልዕኮ ስኬታማ እንዲሆን በትብብር እና በቅንጅት መሥራት ተችሏል፡፡
- Heat Treated Meat Guideline, (EAA livestock product regulatory LEO, EFDA, UNIDO FAO, and Acadamia)
- HACCP Guideline for Heat Treated Meat (EAA livestock product regulatory LEO EFDA, UNIDO, FAO, and Academia)
- Standard for Heat Treated Meat, (EAA, EFDA, MOTR, private campony, Academia and IES)
- HACCP Guideline for Raw meat (EAA and private company)
- የቻይና ተቆጣጣሪ አካላት መጠይቅ መሙላት (MoA, MOTR, EFDA, AHI, LDI,IES, UNIDO እና EAA)
- በሙቀት የተቀቀለ ስጋ ጋይድላይን እና HACCP system implementation በባለድረሻ አካላት ተተችቷል፡፡
- የዶሮ ስጋ እና እንቁላል ጥራት እና ደህንነት ጋይድላይን ዝግጅት(MOA, EAA and Stichining Wagenigen university)

- በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል በመጣ ደብዳቤ መሰረት የኢትዮጲያ ስጋ አምራች ቄራዎች እና ስጋችን እንዲመዘገብ ቤጂንግ ለሚገኘው ኢንባሲያችን ሞልተን ልከናል፡፡
- የማዘጋጃ ቤትና የግል የአገር/ውስጥ ቄራዎችን ከክልሎች ጋር በመሆን መመዝገብና 10 ቄራዎችን ለማየት ችለናል፡፡
- ሌሎች የእንሰሳት ምርቶችን (ወተት፣ ማር፣ እንቁላል፣ዓሣ) ለሚያቀናብሩና ለሚያደራጁ ድርጅቶች ከክልሎች ጋር በመሆን መመዝገብና 15 ድርጀቶች ላይ ለመውጣት ቸክሊስት አዘጋጅተናል፡፡
- የስጋ እና የተረፈ ስጋ ኤክስፖረቱን ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ማለትም ከኤርፖርት ካርጎ፣ ከጎምሩክ ኮሚሽን፣ ከብሔራዊ ደህንነት፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከብሔራዊ ባንክ፣ ከግብርና ሚኒሰቴር፣ ከንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒሰቴር፣ ከኦሮሚያ እስልምና ጉዳዮች፣ ከእንሰሳት ልማት ኢነስቲቲዮት፣ ከቻምበር ኦፍ ኮመርስ፣ ከስጋ አምራች እና ላኪዎች ማህበር፣ ከሁሉም ኤክስፖርት ቄራዎች እና ከቀራ ስርቢስ ተጠቃሚዎች ከድራይብ ፕሮጅቸት ባገኘነው የገንዘብ ድጋፍ  ከሬጉላቶሪ አኳያ ባሉ መልካም አጋጣሚዎች እና ተግዳሮቶች ዙሪያ ውይይት አድረገናል፡፡

**የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት ደረጃ ማሳደግ እና ማሻሻሸል**

- በመደበኛ በጀት በግልጽ ጨረታ ሊገዙ የሚችሉ ግብዓቶችን የመለየትና የግዥ መግለጫ/ስፔሽፊኬሽን በማዘጋጀት የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓት በመጠቀም ጨረታ የማውጣት ሥራዎች ተሰርቷል፣አላቂ የላቦራቶሪ ግብዓት ግዥ ጨረታ አሸናፊ ድርጅቶችን ጋር የውል ስምምነት መፈጸም ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በማዕከሉ የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡
- በተጨማሪም ለሥራ የሚያስፈልጉ የላቦራቶሪ ቋሚ መሣሪያዎችና አላቂ ግብዓቶችን፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ጥገና እና ካሊብሬሽ አገልግሎት ግዥ ፍላጎት የመለየት፣ ዝርዝር የግዥ ስፔስፊኬሽን ሰነድ በማዘጋጀት ለተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ፕሮፖዛል የማቅረብ  በርካታ ሥራዎች ተሰርቷል፡፡

## 4.2 ተግባራዊ የተደረገ የህግ ማዕቀፍ

- የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004፣ የመኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ የክለሳ ስራ ተካሂዷል፡፡
- ከሕግ አገልግሎት ሥራ ክፍል ጋር በመቀናጀት ያለብቃት ማረጋገጫ በመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ንግድ የተሰማሩ ተቋማትን ወደ ህጋዊ አሰራር ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ እንዲቻል ስምሪት ተሰጥቷል፡፡
- የኢንስፔክሽን እና የአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ መመሪያ ድራፍት ለማዘጋጀት ታቅዶ 90% ተዘጋጅቷል፡፡ አፈጻጸሙ 90% ሆኗል፡፡

- ያለማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን መመሪያ እና በእንስሳት ጤና ባለሙያዎች የሚታዘዙ የእንስሳት መድኃኒቶችን መመሪያ በዓቃቢ ህግ ፀድቆ የመጣ ሲሆን የእንስሳት መድሃኒት አስተዛዘዝ መመሪያ ግን እንደ ሞዴል መመሪያ ተደርጎ ለክልሎች እንዲጠቀሙበት ከፀደቀው መመሪያ ጋር የምንልከው ይሆናል፡፡
- የእንስሳት መድሃኒት ምዝገባ መመሪያ በዓቃቢ ህግ በተሰጠው ግብረመልስ መሰረት ተስተካክሎ እንዲጸድቅ ተልኳል፡፡
- ለንግድ ዓላማ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት ልዩ ፈቃድና ቁጥጥር መመሪያ ተዘጋጅቶ በዓቃቢ ህግ እንዲጸድቅ እንዲላክ ለህግ ክፍል ለመላክ በዝግጅት ላይ ነን፡፡
- ለግብርና ሚኒስቴር ቀርቦ የነበረዉንና የእፅዋት ጥበቃ ስራን ባካተተ መልኩ ይሰራ ተብሎ ወደኃላ የተመለሰዉ የእጽዋት ኳራንታይን አዋጅ የእፅዋት ኳራንታይንና የእፅዋት ጥበቃ አዋጅ በሚል ተስተካክሎ ለፍትህ ሚኒስቴር የተላከ ሲሆን በዚህ ሩብ ዓመት ፍትህ ሚኒስቴር የተሰጠውን አስተያየት ከግብርና ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለሙያዎች፣የስራ ሀላፊዎች፣ህግ ክፍሎች፣ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የተሰጠውን አስተያየት ከፍትህ ሚኒስቴር ለመጡ ባለሙያዎች በማስረዳት የጋራ መስማማት ላይ ተደርሷል በተደረሰበት ስምምነትም ለሚመለከተው አካል እንዲላክ እየተሰራ ነዉ፡፡
- Multisectoral National One Health Food Safety Technical Working Group (NOH-FSTWG) በጋራ በመሆን
    - ✓ Draft Action Plan for 2017 Ethiopian Fiscal Year (EFY) የአንድ አመት እና Draft Guiding Document (2024/25 - 2029/20230) ተዘጋጅተዋል፡፡
- ያልተዘጋጁ እና በከፊል የተዘጋጁ የእፅዋትና የእፅዋት ውጤቶች ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር የወጣ አዋጅ (Proclamation to primary and semi processed agricultural produce quality and safety) ድራፍት ተዘጋጅቷል፡፡
- የብቃት ማረጋገጫ መመሪያ መነሻ ድራፍት ተዘጋጀቶዋል::
- የዕፅዋት ካራንታይን ማኑዋል ተዘጋጅቶ እንዲታተም ተልኳል::
- የሀገር ውስጥን የአመራረት ስርዓት ለማስተካከል እና ለማሻሻል እንዲሁም የምርትን ዱካ ለመለየት የሚያግዝ እና ጤናማ የምርት ሰንሰለት እንዲኖር የሚያስችል ETHIO-GAP የሚል ርዕስ ለሆርቲካልቸር ማለትም ለአትክልትና ፍራፍሬ ተክሎች የአለም አቀፍን መልካም አመራረት ስርዓት መመሪያ/ጋይድላይን (GLOBAL GAP) ተከትሎ ዶክመንት በመደራጀት ላይ ነው፡፡

- የአገለግሎት ክፍያ ደንብ ማሻሻያ እንዲደረግበት በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በስራ ክፍሉ የሚሰጡ አገልግሎቶች ማሻሻያ ተደርጎ ለሚመለከተው ኮሚቴ ተልኳል::
- ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የመጣውን የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አሰጣጥ ደንብ ላይ አስተያየት ተሰቷል።
- የፀረ-ተባይ ኢንስፔክሽንና የተቋማት ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ እና በህግ ክፍል ታይቶ በጋዜጣ ላይ ለባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡበት ማስታወቂያውን ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል።
- የፀረ ተባይ እና ማዳበሪያ ፍቱንነት ሙከራ አሰራር-ሂደት የመጀመሪያ ድራፍት ላይ ከባለድርሻ ከካላት ጋር ዉይይት ተደርጎ እና ተተችቶ የጋራ የመግባቢያ ሰነዱ ረቂቅ ወደ ፊርማ ከመኬዱ በፊት የህግ አገልግሎት ስራ አስፈፃሚ እንዲያየው ተልኳል።
- የአፈር ማዳበሪያና ጤንነት ማሻሻያ ግብአት ምርት ግብይትና አጠቃቀም ቁጥጥር ረቂቅ አዋጅን አሁን ካለው የተቋማት ስልጣንና ተግባር አንፃር በማየትና ማብራሪያ በማዘገጀት ወደሚመለከተው ቀጣይ አካል (ግብርና ሚኒስቴር) ተልኮ ለቀጣይ ምላሽ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።
- የስነ-ህይወታዊ ፀረ-ተባይ ጊዜያዊ መስፈርትን በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲተች ተደርጎ ዳግም ረቂቁ ተከልሶ የመጨረሻውን ረቂቅ እንዲፀድቅ ለውሳኔ ለኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ማኔጅመንት ቀርቧል።

## 4.3 በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (Digitalization) የታገዘ አገልግሎት

- 3በእንስሳት መድሃኒት ሬጉላቶሪ ስር ያሉ አገልግሎቶችን በ ድህረ ገጽ እንዲከናወኑ(ዲጂታላይዝድ) እናደርጋለን ብለን አቅደን 17 አገልግሎቶችን በኢሰርቪስ እንደሰጡ አድርገናል። አፈጻጸሙም 100% ሆኗል።
- የዲጂታላይዜሽን ኮሚቴ በሥራ ክፍሉ በዲጂታል ሰርቪስ እየተሰጡ ያሉ እና መስጠት ያልተጀመሩ አገልግሎቶችን በመለየት ለሚመለከተው አካል ተልኳል:: ከዚህም ዉስጥ በፍጥነት ወደ ስራ መግባት ያለበት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ‘COC‘ አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን ዲጅታላይዝድ ለማድረግ ( በE-service ) ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመሆን በተመረጡ 3 አገልግሎቶች ላይ ተፈላጊው መረጃዎች ተደራጅተው ለስልጠና እንዲዘጋጁ ተደርጎዋል::
- ‘E-Phyto‘ የዲጂታላይዜሽን በሚመለከት፡-
    - ለማስጀመር 15 Laptop, 3 desktop, 2 printer, 15 telephone እንዲገዛ ለTMA ጥያቄ ቀርቦ በግዥ ሂደት ላይ ይገኛል።
    - የኔዘርላድ ኢምባሲ የ ኢ ፋይቶ ስራን ለማገዝ ባዘጋጀው የውይይት መድርክ በ የግብርና ባለስልጣን ትሬድማርክ አፍሪካ እንዲሁም ስራዉን ለመስራት

ያሸነፈዉ ድርጅት (Brisk solution) በተገኙበት ከኔዘርላንድ በመጡት በስራዉ ከፍተኛ ባለሙያና አማካሪ በሆኑት ስለስራውና በቀጣይ ልንከተለዉ ስለሚገባ አካሄድ ውይይትና ገለጻ ተደርጎዋል::

- "ePhyto Solution" ከአለም አቀፍ የዕፅዋት ጥበቃ ስምምነት (IPPC Hub) ለማገናኘት Account ተፈቅዶልን ተጫራቹ ድርጅት የኢንትግሬሽን ስራ የተጠናቀቀ ሲሆን የሙከራ ስልጠና ለመስጠት በዝግጅት ላይ ይገኛል ፤ በተጨማሪም ከኢትዮቴሌኮም ጋር ክላዉድ ሆስቲንግ የማዘጋጀት ስራ ተጠናቋል ፤ ሲስተም የመጫን ስራ እየተሰራ ይገኛል እንዲሁም 'SMS Short Codes' የሚሆን አገልግሎት ለማስገባት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

- ከሳይንስ እና ኢኖቬሽን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ሁሉንም የፀረ-ተባይ ማዳበሪያ አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ በማድረግ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ያለው የወረቀት አልባ አገልግሎት መስጠት ተጀምሯል።

➢ ከኢኖቬሺንና ቴክኖሎጂ ሚኒሰቴር ጋር በመተባበር በመኖ ሬጉላቶሪ የሚሰጡ 6 አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ለማድረግ

✓ ለመኖ ምርት ምዝገባ

✓ ለመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃለ አስመጪ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀ

✓ ለመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃለ ላኪ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

✓ ለመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች ድርጅት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

✓ ለቅድመ ማስወጫ ሰርተፊኬ፣ የጥያቄ ማቅረቢያና አስፈላጊ መስፈርቶች ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል

✓ ሥራውን በባለቤትነት በትኩረት የሚከታተልና መረጃ ሲጠየቅ በጊዜው የሚሰጥ ሰው ተመድቧል

✓ ሥራውን የተሳለጠ ለማድረግ የቴሌግራም ግሩፕ ተከፍቷል ።

**መረጃ ማጠናከር**

➢ 3 ጊዜ የተመዘገበ የመኖ ንግድ ተቋም፣ ባለሙያ፣ መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መረጃዎችን በየወሩ ለማደራጀት ታቅዶ የተከናወነ ሲሆነ አፈጻጸሙ 100% ነው።

➢ በእንስሳት መኖ ንግድ ስራ ዘርፍ ለመሰማራት በመፈለግ ከስራ ክፍሉ መረጃዎችን ለመውስድ ለሚቀርቡ 15 ተገልጋዮች ተገቢውን መረጃ ለመስጠት ታቅዶ ለ18 አገልግሎቱን ፈልገው ለሚመጡ ተገልጋዮች የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው።

- 30 የመኖ ማምረቻ ተቋማትን የምርት መረጃ ለማሰባሰብና ለማደራጀት ታቅዶ ከ 29 ድርጅቶች መረጃ የተሰባሰበ ተሰባስቧል። አፈጻጸሙ 96.67 % ነው።
- ከ 15 የመኖ ጥሬ ዕቃ ማምረቻ ተቋማት አመታዊ የምርት መረጃ በአካላዊ ምልከታ እና ከሰነድ ቋታቸው ማመሳከርና ለማረጋገጥ ታቅዶ ከ12 ድርጅቶች መረጃ የተሰባሰበ ተሰባስቧል። አፈጻጸሙ 80 % ነው።
- ከ10 የመኖ ግብዓት አስመጪ ተቋማት የምርት መረጃ ለማደራጀት ታቅዶ 100 % ተከናኗል።
- በ7 የመኖና የመኖ ግብዓት ላኪ ተቋማት ከሀገር የወጣ የምርት መረጃ ለማደራጀት ታቅዶ 100 % ተከናኗል።
- የላቦራቶሪ ቴክኒካል ሥራዎችና ተያያዥ መረጃዎችን በሰነድ እና በኤልክትሮኒክስ የማደራጀትና የመረጃ አቅርቦት ስርዓት ምቹና ቀልጣፋ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሠረት፤ እንደ ተቋም የተቀናጀ የላቦራቶሪ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት እስከሚዘረጋ ድረስ፤ ጎግል ድራይብ/ሼር በመጠቀም መረጃዎችን የማደራጀት፣ ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች እና አመራሮች በማጋራት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል።
- በዚህም መሠረት የጎግል ሽትን በመጠቀም (1) ቋሚ እና አላቂ የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ቆጠራ እና ማቀናነሻ (2) የላቦራቶሪ ግብዓት ግዥ ፍላጎት ማሳወቂያ እና የግዥ ፍላጎት ወይም ስፔስፊኬሽን ማዘጋጃ እና መገምገሚያ (3) የመድኃኒት ጥራትና ደህንነት ምርመራ ሥራ ሂደት መከታተያ (4) የመኖ ጥራት እና ደህንነት ምርመራ ሥራ ሂደት መከታተያ (5) የእንስሳት ምርት ጥራት እና ደህንነት ምርመራ ሥራ ሂደት ከመታተይ (6) የናሙና ቅበላና ምዝገባ እና የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት (7) የቴክኒካል የምርመራ ሥራ ሪከርድና ተያያዥ ሰርቲፊኬት መረጃ ማደረጃት ተችሏል።
- የምርመራ ሥነ-ዘዴዎች እና ተያያዥ መረጃዎች፣ የጥራት ማኔጅመንት የአሰራር መመሪያዎች እና ተያያዥ መረጃዎች እንዲሁም የማጣቀሻ መጽሐፍትና ጋይድላይን መረጃዎችን ኤሌክትሮኒክስ ዳታ በወረቀት ሕትመት የማደራጀት እና አገልግሎት ላይ የማዋል ሥራዎች ተሰርተዋል።
- PCE tool'ን ተግባራዊ ለማድረገ የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ 'Country profile' እና 'Inception report በTCP/ETH/4003 and MTF/ETH/139/STF-F Projects' የበጀት ድጋፍና በFAO አስተባባሪነት የባለስልጣኑ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች፣ የክልል ግብርና ቢሮ፣ የክልል ተቆጣጣሪ እና ባለድረሻ አካላትን በተገኙበት የሁለት ቀን 'In inception Workshop' በማካሄድ 'NPPO organization structure' እና 'Resource' መረጃ በጋራ መሙላት ተችላል።

- የሰሊጥ መልካም አመራረት እና አያያዝ (GAP &GHP) ማንዋሎች ተዘጋጅተው ለመጨረሻ ቫሊዳሽን ተዘጋጅተዋል፡፡

**የተሰበሰበ ጠአገልግሎት ክፍያ**

- ከመኖ ተቋማትና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ፣ ዕድሳት፣ ምትክ አሰጣጥ የሚሰበሰበውን የአገልግሎት ክፍያ ብር 35500 መረጃ ለመስጠት ታቅዶ፣ ብር 66021.20 ከተሰጠው አገልግሎት ወደ ተቋሙ የሂሳብ አካውንት መግባቱ የተረጋገጠ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ በዚህ ስድሰት ወር ለመሰብሰብ ከታቀደው 63900 ብር 145136.80 ማሰባሰብ ተችሏል፡፡

## የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል

## የሰው ሀብት ሙሌት

- በተለያዩ ዘዴዎች የሚቀርቡ የማስረጃ ጥያቄዎችን 100% ለማስተናገድ ታቅዶ ለቀረቡ ጥያቄዎች ሙሉ ለሙሉ ማስረጃ ተሰጥቷል፡፡
- በዚህ 6ወር 2 ሠራተኛ ከጡረታ ማስከበር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራትን ለማከናወን ታስቦ የ5 ሠራተኞች የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ሲሆን ከፍ ያለበት ምክንያት የ3ቱ ሠራተኛ ከዚህ በፊት መውጣት የነበረባቸው ግን ፕሮሰስ ባለማድረጋቸው ዘግይቶ አሁን ላይ የተከናወነ ነው፡፡
- በዚህ 6ወር ቅጥርና ዝውውርን በተመለከተ 1 የኮንትራት ቅጥር እና 1 ቋሚ ቅጥር የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 28.57% ነው፡፡ ዝውውር 1 የተደረገ ሲሆን ሌሎች በበጀት እና በተለያዩ ምክንያቶች የዘገየ ቢሆንም በአሁኑ ሰአት ለፈተና ተጠርተዋል 75% ተከናውኗል፡፡
- በሚቀርቡ የቅሬታና የዲሲፕሊን ጉዳዮች ላይ በየጊዜው የክትትል ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን በዚህ ሩብ አመት ምንም አይነት ቅሬታ የቀረበ የለም፡፡

## በስልጠና የተገነባ የሰው ኃይል

- በዚህ 6ወር በተለያየ ዘዴ የመፈጸም አቅምን ለማዳበር የሚያስችሉ ትምህርትና ስልጠናዎችን ማመቻቸት፣መከታተል፣መደገፍ እና መገምገም 100% ታቅዶ ተከናውኗል
- የግንዛቤ ማስጨበጫ በውጤት ተኮር እቅድና ውጤት አሞላል ዙሪያ ለ 63 ወንድ 37 ሴት በድምሩ ለ100 ከዋናው መ/ቤት፣ ከማእከላዊ ማእከል እና ቃሊቲ ላብራቶሪ ለተውጣጡ ሰራተኞች ተሰጥቷል ፡፡
- ለ6 ሠራተኞች ኢፍሚስ፣ ለ14 ሠራተኞች በአይሶ 31000 ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

## ቀልጣፋ የሪከርድ፣ የመረጃና የማህደር አገልግሎት

- በዚህ 6ወር 3 ጊዜ የሰራተኞችን መረጃዎች፣ በኮምፒዩተር ሲስተም መዝግቦ ማደራጀት ፣ የመረጃ ቋቱን የመከለስ ሥራ ታቅዶ 100% ተከናውኗል፡፡
- በአመቱ ወጪና ገቢ ደብዳቤዎችን ለሚመለከታቸው አካላት 100% እንደደርሱ ለማድረግ ታቅዶ ከ100% በላይ የተከናወነ ሲሆን በዚሁ መሠረት 3,991 ወጪ 366 ገቢ እንዲሁም 2,784 የፋይል እንቅስቃሴ ሥራ ተሰርቷል፡፡

## የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ሪፖርት ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ-መልስን ማሻሻል

- እስከዚህ ሩብ ዓመት የተሻሻለ የእቅድ ፣ ሪፖርት ዝግጅት ግምገማና መረጃ አስተዳደር ሥራ በዕቅዱ መሠረት 100% ተከናውኗል፡፡ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል፡-
  - ✓ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድን ከመካከለኛ ዘመን የግብርና ሴክተር ዕቅድ ጋር የማናበብ ስራ ተከናውኖ ዕቅዱን ለከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች የማስተዋወቅ ስራ ተከናወኗል፡፡
  - ✓ የ2014-2016 ዕቅድ ክንውን (የ3) ዓመት የሪፖርት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
  - ✓ ለሪፎርም ስራዎች የሚፈለጉ የባለስልጣኑን የዕቅድና የክንውን ሰነዶች በሀርድና በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡ በስራ ክፍሉ የመረጃ ቋትም እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡
- በዚህ 6ወር 2 ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ እቅድና ሪፖርት ሰነድ የማድረግ ስራ ተከናውኗል ፡፡ እስከዚህ በሩብ ዓመቱ 6 ጊዜ ከተከናወኑ የዕቅድና ሪፖርት ሰነድ ዝግጅት ስራዎች መካከል ፡-
  - ✓ የባለስልጣኑ ቁልፍ ተግባራት ዕቅድ
  - ✓ የባለስልጣኑ ዝርዝር ተግባራት ዕቅድ
  - ✓ የ2017 ዓመታዊ የፕሮግራም በጀት ሪፖርት
  - ✓ የ2017 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት የድርጊት መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡
- በዚህ 6ወር 2 በምስራቅ ማዕከል እና በደቡቡ ማዕከል የክትትልና ግምገማ አሰራር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ የተከናወነ ሲሆን እስከዚህ ሩብ ዓመት 4 ከተደረጉ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች መካከል፡-

በምስራቅ ማዕከል እና በደቡቡ ማዕከል በአዳማ ጣቢያ ' እና በሐዋሳ ቅርጫፍ ማዕከል የተደረጉ የዕቅድ ክትትል እና ድጋፍ ስራ የሚገኝበት ሲሆን የክትትልና ድጋፊ ሪፖርትም ለሚመለከተው ቀርቧል፡፡

- ✓ በዚህ መሠረት የፊዚካል ስራዎችንና የበጀት ዕቅድን የጋራ የማድረግ ስራ ታይቷል፡፡

- ✓ ዕቅድ በየደረጃው እስከታችኛው ፈጻሚ ድረስ እየወረደ መሆኑ ካስጌድ መደረጉ ታይቷል፡፡

- ➢ በዚህ 6ወር 2 የበጀት እና እቅድ አፈጻጸም ትግበራ ክትትልና ግምገማ ስራ ተከናወነ ሲሆን እስከዚህ ሩብ ዓመት 4 ተከናውኗል ፡፡ ይህም ስራ ክፍሎች የተያዘላቸውን በጀት ከስራ ጋር የተጣጣመ 1:1 መሆኑን ክትትል በማድረግ ለመደገፍ የተከናወነ ነው፡፡ በዚህ መሠረት
  - ✓ በዚህ 6ወር በአዲሱ የተጨመረው የቋሚ ሰራተኛ የደሞዝ ልዩነትና ሰብአዊ ለሆኑ አገልግሎቶች ወጪዎች እጥረት ላለባቸው የስራ ክፍሎች የበጀት ልዩነቱን በመግለጽ ተጨማሪ በጀት እንዲጠየቅ ለገንዘብ ሚ/ር ማብራሪያ በመስጠት ግብረመልስ ተሰጥቷል፡፡
  - ✓ በዚህ 6ወር 2 ጊዜ ለእንስሳት ላብራቶሪ እና ለእጸዋት ላብራቶሪ የበጀት ዝውውር ተደርጓል፡፡
  - ✓ የእንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ፕሮጀክት በጀት ወደ ግብርና ሚ/ር እንዲዛወር በተደረገው ስምምነት መሠረት የበጀት ዝውውር እንዲፈጸም ተደርጓል፡፡
  - ✓ የ2017 በጀትን በሁሉም ፕሮግራሞችና የወጪ ርዕሶች በሲስተም የመመዝገብ ስራዎች ተጠናቀው ለበጀት ቁጥጥር ስራ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡
- ➢ የፕሮጀክቶችን ስራዎችን የመከታተልና የመደገፍ ስራዎች ተከናውኗል፡፡ ይህም በተለይ በምግብ ስርዓት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት የተከናወነ የክትትል ስራን የተመለከተ ሲሆን በፕሮጀክቱ ዕቅድ መሠረት የስራ ክፎሎች ላቀረቡት የድጋፍ ጥያቂ አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡

## የፋይናንስና ግዥ አስተዳደር ማሻሻል

## የተመደበውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል

- ➢ አመታዊ ፣ ሶስት ወር እና ወርሃዊ የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ ለማቅረብ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡
- ➢ የሚቀርቡ የክፍያ ጥያቄዎችን በተፈቀደውና በቀረበው በጀት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት የበጀት ማረጋገጥ ስራዎችን ተሰርታል፡፡
- ➢ በየወሩ ገቢ እና ወጪ መሰረት ያደረገ የበጀት መረጃ ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት የ5 ወር ምዝገባ ተከናውኗል፡፡
- ➢ የበጀት አጠቃቀም መረጃ ለስራ ክፍሎች በየወሩ ለማድረስ ታቅዶ የአምስት ወር የተዘጋጀ ሲሆን አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡

- ከተለያየ ምንጮች የሚገኙ የአገልግሎት ገቢዎችን በግማሽ አመቱ ብር 500,000. /አምስት መቶ ሽህ/ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 625,635.63 የዕቅዱ 125.12 % ለማከናወን ተችሏል፡፡
- በስራ ኃላፊች ተፈቅደው እና በጀታቸውን ተረጋግጦ የሚቀርቡ ክፍያዎች 100 ፐርሰንት ከጥሬ ገንዘብ ንክኪ የጸዳ የኤልክትሮኒክ ክፍያ ለመፈጸም ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት 100 % ተከናውኗል፡፡
- የተከፈሉ ቅድመ ክፍያዎችን በወቅቱ እንዲወራረዱ በተደረው ክትትል መሰረት 100 ለማወራረድ ታቅዶ 95 % እንዲወራረድ ሆኗል፡፡
- ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀት እና ለገንዘብ ሚኒስቴር ለማቅረብ 5 ጊዜ ታቅዶ 4 ጊዜ የቀረበ ሲሆን አፈጻጸሙ 80 % ሆኗል፡፡
- ከተለያዩ ግዥዎችን የሚሰበሰቡ የተጨማሪ እሴት ታክስና ዊዝሆልድ የተቀነሱ (የተሰበሰቡ) ክፍያዎችን በማጣራትና በማደራጀት በወቅቱ ገቢ ለማድረግ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት 100 % ተከናውኗል፡፡
- ከሚሴ ካራንቲን ጣብያ የአገልግሎት ክፍያ ብር 153,460,743.11 የተሰበሰበ ሲሆን 100 % ተከናውኗል፡፡
- በኤሌክትሮኒክ እና በሃርድ ኮፒ ክፍያ የተፈጸመባቸው ሰነዶች ማደራጀትና በሰነድ ክፍል በአግባቡ ለመያዝ በታቀደው መሰረት ሙሉ ለሙሉ ተናውኗል፡፡
- በመ/ቤት ደረጃ ለገጠመው ከፍተኛ የበጀት ጉድለት ከተለያዩ ፕሮግራሞች የበጀት ዝውውር ተከናውነዋል፡፡
- የመንግስት የሠራተኞች የደመወዝ ማሻሻያ ለሁሉም ሠራተኞች ተግባራዊ ተደርጋል፡፡

## ነቀፊታ ያለበትን የኦዲት ግንኙትን መቀነስ

- የክፍያ እና የግዥ ሰነድ አፈፃፀም የአሰራር ስህተት እንዳይኖር ከመፈጸሙ በፊት ተጣርተው እንዲፈጸሙ እና ከግኝት የጸዳ እንዲሆን ክትትል ተደርጋል፡፡
- በሚቀርቡ የኦዲት ግኝቶች ላይ ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ በታቀደው መሰረት አንድ ጊዜ የተሰጠ ሲሆን ሁለተኛው በግማሽ አመቱ መጨረሻ ሲቀርብ ምላሽ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

## የመንግስት የኤሌክትሮኒክስ ክፍያን በመቀጠም ወቅቱን የጠበቀ እና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት

- የተከናዎኑ ዝርዝር ግዥዎች ለዋና መ/ቤት እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የቢሮ ኪራይ በውሉ መሰረት ብር 33,019,066.35 ለነዳጅ ግዥ 3,908,706.48 ፣ ለጥገና አገልግሎት እና መለዋወጫ ዕቃ ግዥ ብር 2,276,978.48፣ ለጽ/መሳሪያ እና ጽዳት ብር 919,958.66.፣ለደንብ ልብስ ግዥ ብር 1,218,876.93 ለኢንሹራንስ ብር 2,178,702.25

አገልግሎት ክፍያዎች ብር 1,207,584.17፣ ብር 811,097 ያልተጠቀሱ ጥቃቅን ወጪዎችን በድምሩ በዚህ ግማሽ ዓመት ብር 45,540,970.32

- የተቋሙን ግብአት አቅርቦት ለማሳደግ በዋጋ ማቅረብያ እና በማዕቀፍ የሚቀርቡ ግዥዎችን ለማከናወን ታቅዶ 68% የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙን ዝቅ ያለበት ምክንያት የማዕቀፍ ግዥ የሚቀርቡ ግዥዎችን በተሟላ መልኩ ባለመቅረቡ ነው፡፡

## የመንግስት የኤሌክትሮኒክ የግዥ ስርዓት ለመጨመር የተከናወኑ ዋናዋና ተግባራት

- የተቋሙን አመታዊ የግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት ማጸደቅና በድህረ ገጽ ይፋ ለማድረግ ታቅዶ በእቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡
- በግማሽ አመቱ ሁለት የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ አንድ የደንብ ልብስ እና አንድ የህትመት የጨረታ ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን በድምሩ ሁለት ሰነድ ዝግጅት በእቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡
- ግዥዎች በ electronic government procurement system በተሟላ መልኩ ለመተግበር ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ሙሉ ለሙሉ ተተግብሯል፡፡
- የሠራተኛ መታወቅያ፣ ባጅ፣ የጠረጴዛ ስምና የስራ ድርሻ የሚያመላክት የህትመት ስራዎችን ለማከናወን ከሁለት ድርጅቶች ጋር ውለታ የተገባ ቢሆንም በውሉው መሰረት ለመጨረስ የማረጋገጥ ስራዎች ይቀራሉ፡፡
- የውል እድሳት የሚያስፈልጋቸው የቢሮ ኪራይ እድሳት ከማድረጋችን በፊት በተለያየ ውል እና ክፍል የነበሩ ቢሮዎች ወደ አንድ ማእከል በማደራጀት አንድ የቢሮ ክራይ ውል እንዲዘጋጅ ተደርገዋል፡፡
- ውል የሚያስፈልጋቸው የአገልግሎት እና የዕቃ ግዥ የውል ሰነድ በማዘጋጀት እንዲጸድቁ ተደርጋል፡፡
- በእቅድ ያልተካተቱ ጥቃቅን ግዥዎች እና ከአንድ አቅራቢ የሚቀርቡ የነዳጅ ኩፖን እና አቢሲንያ ካርድ ግዥዎችን ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል
- የተለያዩ ግዥዎችን ውል፣ የዋና መ/ቤት እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቢሮ ኪራይ ውል፣ የጥገና ውል እና ሌሎች ተያያዥ ውሎችን ተፈፃሚነታቸውን ለመከታተል በተያዘው ዕቅድ የተከናወነ ሲሆን በበጀት ዕጥረት ምክንያት ውል ያልተያዘላቸው የድሬዳዋ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ይገኙበታል፡፡
- ለቢሮ ውበት አገልግሎት የሚውሉ ችግኝና የአበባ መትከያዎች ግዥ ተፈጽሞ ስራ ላይ ውለዋል፡፡

## መሠረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል

## የኤሌክትሮኒክስ የንብረት ቁጥጥር ስርዓት በአግባቡ መተግበር 85 %

- 23700 ንበረቶች በተለያየ መንገድ ወደ ንብረት ክፍል ሲመጡ ቆጥሮና ለክቶ በሲስተም የመረከብ ሥራ ለመስራት ታቅዶ 26933 (114% ) ተከናውኗል
- 23700 ንብረቶች ለአገልግት በሲስተም ወጭ እንዲሆኑ ሲፈቀድ ወጭ የማድረግ ሥራ ለመስራት ታቅዶ 25649 (108%) ተከናውኗል
- 80% የክፍሉን ፍላጎት በመለየ የሚያስፈልገው ግብአት ብቻ ለይቶ ለግዢ ማለቅረብ ታቅዶ 80 ስለተከናወነ አፈጻጸሙ 100% ነዉ፡፡
- 132 የነዳጅ (የተሞላ አቢሲኒያ ካርድ) መረከብና ማሠራጨት መረጃዎችን የመከታተል ሥራ ለመስራት ታቅዶ 132 ስለተከናወነ አፈፃፀሙ/100%/ ተከናውኗል
- የንብረት ስርጭትን ግልጽና ፍታዊ ለማድረግ በስርጭት ወቅት ሁሉም እንዲያዉቀዉ በዉስጥ ማስታወሻ ቦርድ ላይ እንዲ ለጠፍ ተደርጓል
- የንብረት ቆጠራ ተካሂዶ በአሁኑ ስዓት ተጠቃሚዎችን የማስፈረም ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- የሚወገዱ ንብረቶችን የመለየት ስራ ተከናዉኖ ለማስወገድ ገማች ኮሚቴ ተመርጦ በሂዴት ላይ ነዉ፡፡

## የመኪና ሥምሪት ሥራን መከታተል እና መተግበር 96% ተከናውኗል

- 1000 የከተማ ሰርቪስና መስክ አገልግሎት ስምሪት ለመስጠት ታቀዶ 1012 ስለተከናወነ አፈጻጸም 101%/ ተከናውኗል
- ለ 30 ተሽከርካሪዎች ከባድ እና ቀላል ጥገና ለመስጠት ታቀዶ 42 ስለተከናወነ አፈጻጸም 140%/ ተከናውኗል፡፡
- ለ50 መኪና ቦሎ የማሠራት ሥራ ለመስራት ታቅዶ በአጠቃላይ ለ29 መኪና ቦሎ የማሠራት ሥራ (58%)ተከናውኗል፡፡ ቀሪዉ ያልተከናወነዉ ወቦሎ ማስደረጊያ ጊዜ ባለመድረሱ በቀጣይ ወር የሚከናወን ይሆናል፡፡
- ለ500 ነዳጅ የሚቀዱ መኪኖችን ተከታትሎ መቅዳትና መቆጣጠር ለማከናወን ታቅዶ 470 ስለተከናወነ (92%) ተከናውኗል
- ለ500 የመኪና ኪሎ ሜትር የመመዝገብ ሥራ ለመስራት ታቅዶ 470 ስለተከናወነ (92%) ተከናውኗል
- 6 መኪና ላይ ጉዳት ሲደርስ ክሌም መሙላትና የመከታተል ሥራ ለማከናወን ታቅዶ 4 ስለተከናወነ (67%) ተከናውኗል፡፡
- 6 ወርሀዊ የነዳጅ ፣የዘይት፣ቅባትና ጥገና ወጭ አጠቃቀም ሪፖርት ለግዥና ንብረት ባለስልጣን ሪፖርት ለማድረግ ታቅዶ 6 (100%) ተከናውኗል
- 6 ጊዜ የተቀየሩ የመለዋወጫ ዕቃዎች ከጋራዥ አምጥቶ ንብረት ክፍል ገቢ የማድረግ ሥራ ለማከናወን ታቅዶ 6 ጊዜ ቀርቦ ሁሉም ገቢ ሁናል (100%)፡፡

## የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ 85% ተከናውኗል

- 100% የህንጻ ጥገና አገልግሎት ሥራዎች ለማከናወን ታቅዶ 50 ጥያቄ ቀርቦ በተለያዩ ባለሞያዎች እና በህንጻዉ ባለቤት ሰራተኞች 25 ተሰርቷል (50%) ተከናውኗል አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት በሰው ኃይል እጥረት ነው፡፡
- 100% የስራ አካባቢ ጥበቃ አገልግሎቶች በተገቢው መንገድ ለማከናወን ታቅዶ 100% ተከናውኗል
- 100% የቢሮ ጽዳት አገልግሎት በተገቢው መንገድ እንዲሰሩ የማድረግ ሥራ ለማከናወን ታቅዶ 50% ተከናውኗል አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት በሰው ኃይል እጥረት ነው፡፡
- 100% የፎቶ ኮፒ አገልግሎት ለሁሉም ክፍሎች በተገቢው መንግድ ለማከናወን ታቅዶ 100% ተከናውኗል
- ባለስልጣን መ/ቤቱን ጉዳይ የማስፈጸም ሥራዎች ለማከናወን 100 % ታቅዶ 100% ተከናውኗል
- 100% የስልክ ኢንተርኔትና የመብራት እና የዉሀ አገልግሎት ክፍያ 42 ጊዜ ተጠይቆ ሁሉም በወቅቱ የመጠየቅ ሥራ እና እንዲከፍል የማድረግ ሥራ ተሰርቷል(100%)
- የመብራት የዉሀ መቆራረጥን ለማስቀረት በተሻለ ሁኔታ ዝግጁ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል

## የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ለውጤታማነትን ማሻሻል

## የተመሠረተ የመረጃ ሥርዓት

- ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ማከማቻ(ስቶሬጅ) ለማዘጋጀት ከኢትዮቴሌኮም በመከራየት ከዌብሳይትና ከኦንላይን ሲስተሞቻችን የሚሰበሰቡ መረጃ ማከማቻ ክላውድ ሰርቨር ለማዘጋጀት 20 ታቅዶ 20 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 100%ነው፡፡
- የኦንላይን አውቶ የባካፕ ሲስተም ለማዘጋጀት 20 ታቅዶ 20 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡
- የመረጃ ደህንነት ሲስተም ለመዘርጋት የኦንላይን ሲስተሞችን የደህንነት ስራ እና የኮምፒውተር ሲስተሞችን አፕዴት ለማድረግ 20% ታቅዶ 20 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ሆኗል፡፡

## የተመሠረተ ወረቀት አልባ ስርዓት

- ዘመናዊ የሰው ሃብት አስተዳደር ተግባራዊ የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡
- ክላውድ የመረጃ ማጋሪያ እና ማከማቻ ሲስተም ተግባራዊ የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡
- የተሽከርካሪ አስተዳደር ሲስተም ተግባራዊ የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡

- ማንዋል አገልግሎቶችን ወደ አንድ መስኮት እና ኢሰርቪስ ስርአት ለማስገባት በተያዘው እቅድ መሰረት እስከ አሁን 26 አገልግሎቶችን ወደ ኢሰርቪስ ስርአት የገቡ ሲሆን አፈጻጸሙ100% ነው፡፡

## ያደገ አውቶሜትድ ያሰራር ስርዓት

- አዳዲስ በተቋሙ እየለሙ ላሉ ሲስተሞች የdomain name እና የ hosting services በማስጀመር የማልማት ስራውን የማቀላጠፍና የማፋጠን ስራ እየተሰራ ሲሆን በዚህም
  - ✓ ለephyto system domain name “ephyto.eaa.gov.et” የመፍጠር እና cloud hosting ከኢትዮቴሌኮም የማዘጋጀ ስራ ተጠናቆ ሲስተሙን የመጫን ስራ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ከአለም አቀፉ የኢፋይቶ ሲስተም (IPPC Hub) ጋር የማገናኘት ስራ ተጠናቆ ለሙከራ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡
  - ✓ ለስጋ ኢንስፔክሽን ሲስተም “ethiomeat.gov.et” domain mane የመፍጠር እና የሆሲንግ ስራ ተጠናቆ ሲስተሙ ወደ ኦንላይን የገባ ሲሆን ለሁሉም ቁራ ባለሙያዎች ሁለት ዙር ስልጠና ሰጥተናል፡፡
- ዘመናዊ የሰው ሃብት አስተዳደር ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ፕሮጀክት ማናጀሮችና ሃላፊዎች ጋር በአካል በመነጋገር በቀጣይ ለማስጀመር በሂደት ላይ የምንገኝ ሲሆን ከነበረው 40% 38% የተከናወ ሲሆን ፡አፈጻጸም 100%፡፡
- የኤሌክትሮኒክ ተሽከርካሪ አስተዳደር ሲስተም በተመለከተ ጥያቄ ያቀረብን እና በአካል በመነጋገር ላይ ያለን ሲሆን በቀጣይ ወደትግበራ ለማስገባት ከተመረጡ ተቋማት ጋር የእኛንም የማካተትና የማስጀመር ስራ የሰራን ሲሆን ከታቀደው 30%፡ 27% የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸም 100% ነው፡፡
- ክላውድ የመረጃ ማጋሪያ እና ማከማቻ ሲስተም ለማዘጋጀት ታቅዶ የተሰራ ሲሆን ለአሁኑ የኢሜይል ስቶሬጅ አገልግሎት በመጀመሩ ከታቀደው 40% ፡38% የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡

## የሲስተም አስተዳደርና ድጋፍ ስራ

## በኦንላይን የአንድ መስኮት አገልግሎት (Electronic single windows) በተመለከተ

- አዲስ አካውንት የመክፈት፡ User deactivate ማድረግ፡ የስራ ድርሻ በመቀየር (Role change) ከቀረቡ 5 ጥያቄዎች ተከናውነዋል አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡
- የኤሌክትሮኒክ ግዢ ስርአትን በተመለከተ - የተቋሙን የአመታዊ የግዥ ፍላጎት ወደ ኢጂፒ ሲስተም የማስገባት ስራ የተሰራ በመሆኑ እና አዳዲስ አካውንት ለመክፈት፣ ፓስዎርድ ለመቀየር፣የስራ ድርሻ ለመቀየር የመጡ 59 ጥያቄዎች ተከናውነዋልአፈጻጸሙ 100% ነው፡፡

- የኢፍሚስ ስርአትን የማስተዳደር ስራን በተመለከተ፦
- አዳዲስ አካውንት በመክፈት፣የተረሱ ፓስዎርዶች በመክፈት፣የኢፍሚስ ሲስተም የስራ ድርሻ (Role) በመቀየር የመጡ 23 ጥያቄዎች ተከናውነዋል አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡
- የኔትዎርክ ጥገና፡የኮምፒውተሮችና የኔትዎርክ ፕሪንተር ሼሪንግ ስራ የተሰራ ሲሆን፦

ጥገና ከተደረገላቸው መካካል

- የቦሌ ጣቢያ ተከራይቷቸው የነበሩትን ቢሮዎች በመዛወሩ ቀደም ሲል ለየብቻ የነበሩት ሁለት የኢንተርኔት መስመሮችን ወደ አንድ መስመር በማካተት የማዘዋወር ስራ ተሰርቷል፡፡

## ተቋማዊ የሪፎርም ሥርዓት በመጠቀም የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ

- የተገልጋይን እርካታ ማሳደግ 84% ለማድረስ ታቅዶ ከውስጥ እና ከውጭ ከተገልጋዮች የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በተደረገ ውይይት ፣ መጠይቀች አዘጋጅቶ በማሰራጨት፣ መረጃ በመሰብሰብ እና ግብረመልስ በመስጠት ተፈጻሚነቱን መከታተል በዋናው መ/ቤት፣ በማዕከላዊ ማዕከል በሚገኙ ጣቢያዎች እና በምርመራ ማዕከል በተሰበሰበ መረጃ በመመስረት የዕርካታ ደረጃው 83% የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 98.80%ነው፡፡
- ከውጪ እና ከውስጥ ተገልጋዩች የሚነሱ የመልካም አስተዳዳር ችግሮችን መሰብሰብ እና ግብረ መልስ መስጠት ተፈጻሚነቱን ለመከታተል ታቅዶ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 95% ነው፡፡
- የውጪ እና የውስጥ ተገልጋዩች አገልግሎት አሰጣጥ ድጋፍና ክትትል ሥርዓት መዘርጋት ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ድጋፍ እና ክትትል የማድረግ ስራ አንድ ጊዜ የክትትል እና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ተግባራዊ ተደርጉዋል፡ ፡ የተሰራው ስራ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች የታዩ ክፍተቶች ተለይተው ግብረመልስ በቃል እና በጽሁፍ ለሚመለከታቸው እንዲደርሳቸው ተደርጉዋል አፈጻጸሙም 100%፡፡
- ለውስጥ እና ለውጭ ተገልጋዮች የቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብ እና አፈታት ሥርዓት ለማሳወቅ በቁጥር አንድ ጊዜ ለማሳወቅ ታቅዶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ለውስጥ ተገልጋዮች የተሰጠ ሲሆን ለውጭ ተገልጋዮች ለሚመለከታቸው በማስታወቂያ የማሳወቅ ሥራ ተሰርቱዋል አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡

## በተቋሙ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መፍታት

- ለውስጥ እና ለውጭ ተገልጋዩች የቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብ ሥርዓትን ለማሳወቅ ታቅዶ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም100% ነው፡፡
- የሚቀርቡ ቅሬታ እና አቤቱታዎችን መረጃዎች በመፈተሽ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ቅሬታን መቀነስ  ከውስጥና ከውጭ ተገልጋዮች የቀረቡ ቅሬታዎች እና

አቤቱታዎች በሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ለአብነት የውስጥ ተገልጋይ ላይ ጥቅማጥቅም፣ስልጠና ፣የደንብ ልብስ፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ፣ውሀ ፣መብራት በኩል ምላሽ ተሰቷዋል፡፡

- የውጭ ተገልጋይ በተመለከተ ለተገልጋይ አክብሮት መስጠት ፣የኢንስፔክሽን ሰራተኞች ከቅጣት ይልቅ ለስራው ትኩረት ሰጥተው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት ቢችሉ የሚሉ ቅሬታዎች ቀርበው በሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች መልስ ተሰቷልዋል፡፡

## ተቋማዊ ካይዘን ሥርዓት መተግበር

- ከካይዘን ኢንስቲትዩት ጋር ስምምነት ሰነድ በመፈራረም ካይዘንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል እቅድ ማዘጋጀት እና ተግባራዊነቱን ለመከታተል ታቅድ ተከናውኗል፡፡
- ከኢንስቲትዩቱ ጋር ደብዳቤ በመጻጻፍ ስራውን ለማስጀመር ምክክር የተደረገ መሆኑ እና በቀጣይም አብረውን ሊሰሩ ፈቃደኛ መሆናቸው ስምምነት ላይ ተደርሱዋል፡፡
- ባለስልጠናን መ/ቤታችን የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርምከሚተገበርባቸው መ/ቤቶች አንዱ በመሆኑ የስራ ቦታ ምቹ ከማድረግ አንጻር ይህንን ስራ የሚሰራ ኮሚቴ በበላይ አመራር ትኩረት ተሰጥቶት በማደራጀት የስራ ቦታ ምቹ ከማድረግ አንጻር በርካታ የካይዘን ፍልስፍና አሰራር እየተተገበረ ያለ እና ተግባራዊነቱን የመከታተል ስራ ተሰርቷል፡፡
- በዋናው መ/ቤት የቢሮ ካይዘን እሳቤ ማደራጀት በተመለከተ ከካይዘን ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በመ/ቤታችን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና አንድ ጊዜ ተቋማዊ የሪፎም ሥርዓት በመጠቀም የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ ለመስጠት በተያዘው ዕቅድ መሠረት አንድ ጊዜ ስልጠና ተሰጥቱዋል፡፡

## ተግባራዊ የተደረገ የህግ ማዐቀፍ

## የባለስልጣኑሥራዎች በህግ አግባብ እንዲሰሩ ማድረግ

- በባለስልጣን መ/ቤት በሚመለከቱ የሕግ ጉዳዮች ማብራሪያ ለመስጠት ታቅዶ 3 ለሕግ ጉዳዮች ስራ አስፈፃሚ ህጋዊ አስተያየት እንዲሰጥበት ከተለያዩ ስራ አስፈፃሚዎች ለቀረቡለት ጥያቄዎች የተሰጠሲሆን እስከዚህ ሩብ ዓመት 6 ህጋዊ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ የሕግ ጉዳዮች ማብራሪያአስተያየት ከተሰጡበት መካከል ፡፡
    - ✓ ኢንደስትሪያል ኬሚካል የመረጃ አያያዝ በተመለከ
    - ✓ ጂ.ኤ.ም.ቢ.ኤስ በተመለከተ
    - ✓ እቃ ማከማቻ ደረሰኝን በተመለከተ
    - ✓ የጉዞ ቲኬትን በተመለከተያልተወሰደ የዓመት እርፍት ክፍያ
    - ✓ ወደ ስራ ለመመለስ
    - ✓ የማዳበሪያ የላብራቶሪ ፍተሸን በተመለከተ

- ባለስልጣኑን የሚመለከቱ  ህጐች የውል ስምነቶችና ሌሎች ህግ ነክ ሰነዶችን ላይ አስተያየት ለመስጠት ታቅዶ 8 በሩብ ዓመቱ  የተከናወነ ሲሆን እስከዚህ ሩብ ዓመት 11ውሎች አስተያየት ተሰጥቷል ፡፡ከተዘጋጁ ውሎች መካከል
  - ✓ የተሸከርካሪ ጥገና
  - ✓ የኢንሹራንስ የውል ዘመን ዕድሳት
  - ✓ አዋሳ የቢሮ ኪራይ
  - ✓ ጎንደር የቢሮ ኪራይ
  - ✓ ድሬድዋ የቢሮ ኪራይ
  - ✓ በድጋሚ በተዘጋጀ ድሬድዋ የቢሮ ኪራይ
  - ✓ የሕትመት ውል
  - ✓ የቢሮ ኪራይ ውል ከቤቶች ኮርፖሬሽን
  - ✓ ሀዋሳ የቢሮ ኪራይ
  - ✓ ለፓርቴሽን ግንባታ ውል
  - ✓ ከፕሬስ ጋር በጋራ ለመስራት የተገባ ውል ናቸው፡፡
- በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የምክር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለሕግ ጉዳዮች ስራ አስፈፃሚ በቃል የቀረቡለትን የሕግ ምክር ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል፡፡
- ለቁጥጥር ተግባሩ የሚያግዙ አዋጅ ደንብ  መመሪያ  ሕጋዊነቱን ጠብቆ እንዲዘጋጅ ለማድረግ በሩብ ዓመቱ 1 እስከዚህ ሩብ ዓመት 20 የህግ ረቂቅ ህጎች በተለያዩ ጊዜ በመሳተፍ ረቂቅ ህጎቹ ሕጋዊነቱን የጠበቀ እንዲሆን100% ተከናውኗል፡፡
- ዝግጅታቸው ከጨረሱ መመሪያዎችና ደንቦች ስራዎች መካከል ፡-
  - ✓ በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ እና ያለማዘዣ ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር
  - ✓ የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መሣሪያ እርዳታ ቁጥጥር መመሪያ
  - ✓ የእንስሳት መድሐኒት ምዝገባ ረቂቅ መመሪያ
  - ✓ ለንግድ አላማ የማይውል ልዩ ፍቃድ የእንስሳት መድኃኒት ግዥ መመሪያ
  - ✓ የዕፅዋት ጥበቃና ኳራንቲን ረቂቅ አዋጅን በድጋሚ የዕፅዋት ጥበቃ ክፍልን ማካተት
  - ✓ የማዳበሪያና የአፈር ጤንነት ማሻሻያ ግብይት ቁጥጥር ረቂቅ አዋጅ
  - ✓ የዕፅዋት ዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ መመሪያ
  - ✓ ፀረ-ተባይ ምዝገባ መመሪያ
  - ✓ የፀረ-ተባይ ኢንስፔክሽን

- ✓ ሥነ ሕይወታዊ ፀረተባይ ምዝገባ ጊዚያዊ መስፈርት
- ✓ የዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር መመሪያ
- ✓ የዕፅዋት ዘር ብዜት ና ንግድ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና አስተዳደር
- ✓ በሶስተኛ ወገን የዘር ጥራት ቁጥጥር መመሪያ
- ✓ የወደቀ ዘር አጠቃቀምና አወጋገድ
- ✓ የደንብ ልብስ
- ✓ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መመሪያ
- ✓ የትምህርትና ስልጠና መመሪዎች ናቸው፡፡

➢ የህግ ረቂቅ ህጎች በተለያዩ ጊዜ በመሳተፍ ረቂቅ ህጎቹ ሕጋዊነቱን የጠበቀ እንዲሆን ተሰርቷል፡፡አፈፃፀሙም 100%ነው ፡፡

➢ የሕግ ቅርፅ እና ይዘት ኖሮአቸው ዝግጅታቸው የጨረሱ መመሪያዎችና ደንቦችን ተከታትሎ ለሚመለከተው አካል መላክ እንደቀረበ ለመፈፀም ታቅዶ በዚህ ሩብ ኣመት 4እስከዚህ ሩብ ዓመት7 መመሪያዎች ለሚመለከታቸው አካላት ለግብርና ሚኒስቴር እና ለፍትሕ ሚኒቴር አስተያየት እንዲሰጥ ተልከዋል፡፡ከተላኩ መመሪያዎች መካከል

- ✓ የዕፅዋት ዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ መመሪያ
- ✓ በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ እና ያለማዘዣ ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር
- ✓ ፀረ-ተባይ ምዝገባ መመሪያ
- ✓ የዕፅዋት ዝርያ ለቀቃ እና ምዝገባ መመሪያ
- ✓ የማዳበሪያና የአፈር ጤንነት ማሻሻያ ግብይት ቁጥጥር ረቂቅ አዋጅ
- ✓ ሥነ ሕይወታዊ ፀረተባይ ምዝገባ ጊዚያዊ መስፈርት
- ✓ የእንስሳት መድሐኒት ምዝገባ ረቂቅ መመሪያዎች ናቸው፡፡

➢ በሀገር አቀፍ ደረኛ የሚካሄዱ ከህግ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶችና ውይይቶች ላይ በመሳተፍ ለቁጥጥር ተግባሩ የሚሆን የህግ ነክ ግብዓት መስጠት 100%ለማከናወን ታቅዶ በ6 ወር ውስጥ በባለድርሻ አካላት በተዘጋጁ 4 የሕግ ረቂቅን የተመለከቱ ውይይቶች ላይ ከህግ ረቂቂ ውይይት ስራዎች መካከል

- ✓ የመኖ ቴክኒካል ህግ የሙከራ ሰነድ(2)
- ✓ የ.በሽታ አምጭ ተህዋስያን መርዛማ ንጥረነገሮች አስተዳደር ቁጥጥር ረቂቅ አዋጅ
- ✓ የንብ ውጤት ግብይት ረቂቅ አዋጅ
- ✓ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በተመለከ የተከናወኑ ስራዎች ናቸው፡፡

## ባለሰልጣኑን በመወከል የህግ ክርክር ማካሄድ

- አዋጁን ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎችን፤ ደንቦችን በመተላለፍ ወይም በባለሥልጣን መ/ቤቱ ላይ የሚፈፀሙ የፍታብሔር ግድፈት በሚኖሩበት ጊዜ ባለሥልጣን መ/ቤቱን ወክሎ ለመከራከር ታቅዶ በ5መዝገቦች ክርክር ተካሂዷል አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡ ከነዚህም መካከል መዝገቡ እየታየበት ያለበት ፍ/ቤት
  - ✓ አማራ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት
  - ✓ ሲቪል ሰርቪስ ፍ/ቤት
  - ✓ 3ቱ በፌደራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት መዝገቡ እየታየ ያለበት ነው፡፡
- አዋጁን ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎችን፤ ደንቦችን በመተላለፍ ወይም በባለሥልጣን መ/ቤቱ ላይ የሚፈፀሙ ማንኛውም ዓይነት የወንጀል ድርጊት በሚኖሩበት ጊዜ ማስረጃዎችን አደራጅቶ ለተገቢው የፍትሕ አካላት በወቅቱ በማቅረብ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ መከታተል 100% ለማከናወን ታቅዶ በባለድርሻ አካላት በተሰጠ ጥቆማ መነሻነት በፖሊስ በተያዘ አንድ መዝገብ ላይ ክትትል ተደርጓል አፈፃፀሙም 100%ነው፡፡
- የፍርድ ቤት ውሳኔዎች በሚኖሩበት ጊዜ ውሳኔዎቹን በአግባቡ ተከታትሎ ማስፈፀም እንደቀረበ ለመፈፀም ታቅዶ በአንድ መዝገብ ላይ አፈፃፀም ተከፍቷል አፈፃፀሙም 100%ነው፡፡

## የተፈጠረ የግብርና ቁጥጥር የህግ ግንዛቤ

- የባለስልጣኑን አዋጅ መመሪያ እና ደንብ ለመስሪያ ቤቱ ሰራተኞችና ለባለድርሻ አካላት በአዳማ ከተማ ግንዛቤ ለማስጨበጥ 10 ታቅዶ 4 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 40% ነው፡፡ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ከተሰራባቸው ተሳታፊዎች መካከል ፡-
  - ✓ ፖሊስ ዐቃቢያን ሕግና የባለስልጣኑ ስራ አስፈፃሚዎች
  - ✓ በዕፅዋት ዘርፍ ላሉ የተለያዩ ባለሙያዎች
  - ✓ በዕፅዋት ዘርፍ ላሉ የተለያዩ ባለሙያዎች
  - ✓ ፖሊስ ግንዛቤውን ማስጨበጫ የተሳተፉ ናቸው፡፡
- ሕገወጥ ንግድና ዝውውር በሚፈፀምባቸው በተለያዩ ቦታዎች መካከል አዳማ 'ገላን' ቢሾፍቱ' መተሀራ' ዱከም' አዲስ አበባ' ቡራዩ'ሰበታና ሀዋሳ ላይ የማፅዳትሥራ ለማከናወን 14 ታቅዶ 12 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 85% ነው፡፡ የህግ ማስከበር ስራ ላይ ከተሳተፉት ተቋማት መካከል
  - ✓ በመኖ ተቋማት ላይ
  - ✓ በዘር ተቋማት ላይ
  - ✓ በሁለቱም ዘርፎች በሚንቀሳቀሱ የንግድ ተቋማት ናቸው፡፡

## የስነ-ምግባር ግንባታ ውጤታማነት ማሰደግ

- የአለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን ህዳር 29\2017 በመስሪያቤት ደረጃ ለማክበር እቅድ ተይዞ የፌደራል ስነ-ምግበር ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሰነዴዬ አዘጋጅቶ ባለመላኩ ምክንያት አልተከበረም ነገር ግን ኮሚሽኑ ሁሉንም የፌደራል ተቋማት የስነ-ምግባር መከታተያ ስራ አስፈፃሚዎች በተገኙበት 02\04\2017 በአዴዋ ዴል መታሰቢ አዳራሽ ተከብሯል፡፡
- ለሰራተኛው እና አመራር ስልጠና ለመስጠት ታቅደ ስልጠና የወሰደ ከፍተኛ አመራር 2 መካከለኛ  አመራር 17 ተሰታል ፡፡
- የስነ-ምግባር መልእክቶችን ከፌደራል ስነ-ምግባር ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በሚመጡበት ወቅት በቴሌግራም አማካኝነት ተላልፈዋል፡፡

## የሙስና ተጋላጭነት ሥጋት መቀነስ

- በተቋሙ የሚገኙ የስራ ክፍሎች የሙስና ስጋት ደረጃ ተለይቷል
  - ✓ የእፅዋት ዘርፍ
  - ✓ የእንስሳት ዘርፍ
  - ✓ መሰረታዊ አገልግሎት
  - ✓ ግዥና ፋይናንስ ደረጃ የተሰጠው በሚቀርቡ ጥቆማዎች መነሻነት ነው)
- በተቋም በህግ ሀብትና ንብረት እንዱያስመዘግቡ የሚገባቸው ሰራተኞች በጠቅላው ሀብት ምዝገባ ፎርማት ወስደው ሞልተው የመለሱ መሪ ስራ አስፈፃሚ ብዛት 2 ሲሆኑ፤ የመእከል ሃላፊ 1 እና ዳስክ ሃላፊ 2 በዚህ 6ወር ጠቅላላ ሀብት ያስመዘገ ሰራተኞች ብዛት 5 ናቸው

## የሙስና መረጃ አስተዳደር ውጤታማነት ማረጋገጥ

- የሚመጡ የሙስና መረጃዎች ጥቆማዎች መቀበል መተንተን በዚህ ሩብ አመት ታቅድ ነበር ሆኖም ግን የቀረበ ሙስና ጥቆማ የለም፡፡

## ማህበራዊ አካታችነትና የሴቶች ተጠቃሚነት

## ወደ አመራር የመጡ ሴት ሰራተኞች አቅም ማሳደግ

- በዚህ 6ወር በማዕከል ለሚገኙ ሰራተኞች የስርአተ ፆታ ማካተት ፣ የሥራዓተ ጾታ እና ጾታዊ ትንኮሳ የግንዛቤ ስልጠና ለመስጠት 30 ሴት ሰራተኞችን፣6 የጥበቃ ወንድ ሰራተኞችን እና 14 ሃላፊዎችን ያካተተ ስልጠና ተካሂዳል አፈጻጸሙ50% ነው፡፡ አፈጻጸሙም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ስልጠናውን ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ የፋይናንስ ጉዳዩች ባለማለቃቸው ነው፡፡
- በዚህ 6ወር ባለስልጣኑ በሁሉም የስራ ክፍሎች የስርአተ ፆታ ማካተታቸውን እና በባለስልጣኑ ጾታዊ ትንኮሳ እና ሰብአዊ መብት ጥሰትን  መከታተል የሚል የታቀደ ሲሆን የስርዓተ ፆታ ማካተት (Gender Inclusion) ክትትል ለማድረግ ሰራተኞች

ስብጥር መረጃ፣ስልጠና እና ዝውውር፣ የሰራተኞች ዳሰሳ ጥናት ተደረጓል።አፈጻጸሙ 100% ነው።

## የማህበራዊ አካቶ ትግበራን በአካባቢ እና ማህበራዊ ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ለመቀነስ ተግባራዊነቱን መከታተል

- በዚህ 6ወር 5 አምራች(አስመጪ) ተቋማት ጋር ተደራሽ በመሆን አገሪቷ የተቀበለችውን የአካባቢ ተጽእኖ ሥርዓት መተግበራቸውን መከታተል የሚል የታቀደ የአካባቢ ተጽእኖ ምዘና (Environmental Impact Assessment - EIA) ሥርዓት የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ ያሉትን ሕጎችና መመሪያዎች ከመጠበቅ አንጻር የአካባቢ ተጽእኖ ምዘና ተግባራዊ የተደረገ በመሆኑ አፈጻጸሙም 100% ነው።
- በዚህ 6ወር 5 በአምራች ድርጅቶች ላይ ባህላዊ እሴቶች ቅርሶች ወጐችና ልምዶችን እንዲጠበቁ ፣የሰራተኞቻቸውን ጤንነትና ደህንነት እንዲሁም መብት መጠበቃቸውን የመከታተል ሥራ ተሰርታል።
- በዚህ 6ወር ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ በሚሰጣቸው 5 ተቋማት ላይ የማምረቻ መሳሪያዎች ፣ ቴክኖሎጂዎችን በአካባቢና በአየር ንብረት ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ ታሳቢ በማድረግ የተሠሩ የተጽእኖ መቋቋሚያ ስልቶች በመገምገም የቁጥጥር ሥራው አንድ አካል እንዲሆን ማድረግ ስራ ተሰርታል ።
- በዚህ 6ወር 5 ተቋማት የግብርና ግብዓት ወይም ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ ሲውሉ ወይም ሲወገዱ በሠራተኞችና በአካባቢው ማህበረሰብ የጤና ጉዳት እንዳያስከትሉ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ስራ ተሰርታል ።
- አምራች ድርጅቶች ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንፃር በባህላዊ እሴቶች፣ቅርሶች፣ ወጎችና ልምዶች እንዲጠበቁ፤ የሰራተኞች ጤንነትና ደህንነት፣ የስራ ስምሪት መብትና የስራ ቦታ ሰላማዊ ግንኙነት መፍጠር የሚያስችል አሰራር እንዲዘረጉ፣ የአካባቢው ማህበራሰብ ተጠቃሚነትና መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር የግንዛቤ ማስጨበጫ በክትትልና ድጋፍ ተደርጋል ።
- በባለስልጣኑ የሴቶች፣ህጻናት፣ወጣቶችና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ
- በዚህ 6ወር ወላጆቻቸውን በተላያዩ ሁኔታ ያጡ ህጻናትን ለማገዝ የማስተባበር ስራ መስራት የሚል የታቀደ ሲሆን እንደ ባለስልጣኑ ሁሉም ከፍተኛ አመራሮችና የስራ አስፈጻሚዎች እንዲሁም ቡድን መሪዎችና የደስክ ሃላፊዎች በተገኙበት እንዲሁም ባለሙያዎችን በማስተባበር የተለያዩ ብዛት ያላቸው አልባሳት፣13,100.00 ብር፣ እስኪፒርቶ፣ማስታወሻ ደብተሮች በማሰባሰብ ለቁርቆስ ክፍለ ከተማ የሴቶችና ማህበራዊ

ጉዳይ ቢሮ ድጋፍ የሚደረግላቸውን ሁለት ህጻናት አጠቃላይ መረጃ እንዲሰጡን በደብዳቤ ያሳወቅን ሲሆን አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡

- በባለስልጣኑ ውስጥ አስፈላጊውን ቁሳቁስ በማሟማላት አንድ የህጻናት ማቆያ ማዕከል ማቋቋም የሚል የታቀደ ሲሆን እንደ ተቋም አንድ የህጻናት ማቆያ ቦታ ተመቻቸ ሲሆን እና አስፈላጊ የተባሉ ቁሳቁሶችን ለማሟላት ለግዥና ፋይናንስ ስራ ክፍል ግዥ የተጠየቀ ሲሆን አፈጻጸሙም 50 % ነው፡፡
- የተቋቋመውን የህጻናት ማቆያ ተጠቃሚ የሚሆኑ ሴቶችና ህጻናትን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ የሚል ታቅዶ የነበረ ሲሆን 18 ህጻናት የተለየ እና የህጻናት ማቆያ መተዳዳሪያ ደንብ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ስንሆን አፈጻጸሙም 50% ነው፡፡
- በዚህ 6ወር በተቋም ውስጥ በቅጥር፣ በደረጃ እድገት፣ በስልጠና፣ በትምህርት ዕድል እና በሠራተኛ ድልድል ወቅት አዎንታዊ ድጋፍ ተደርጋል፡፡
- በዚህ 6ወር በመስሪያ ቤቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ዘርፍ የተደራጁ ሴቶችና ወጣቶችን ተክሞሮአቸውን ማስፋትና፣ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ታቅዶ የስራ ፈጠራ አስተሳሰብ እና ክህሎት ማሳደግ ስልጠናዎች ለ60 ሴት ሰራተኞች የተሰጠ እና አዳዲስ ስራዎችንም ለመስራት የተነሳሱበት በሃይላንድ እና በወረቀት ስራ የተሰማሩ ላይ ስራቸውን የሚያሰፉበት እዲል ያገኙበት ነው እንዲሁም የተደራጁ ሴቶችም ሆነ አዳዲስ ሃሳቦችን የሚያገኙበት የቴሌግራም ግሩፕ ተከፍቶ ሃሳቦችን እያገኙበት የሆን ሲሆን በተጨማሪም ዝቅተኛ ተከፋይ ሴት ሰራተኞች ተደራጅተው ቡና እንዲያፈሉ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተመቻቸ በመሆኑ አፈጻጸሙም 100% ነዉ፡፡
- ለባለስልጣኑ ሰራተኞች ኤች. አይ ቪ. ኤድስ እና ተላላፊ በሽታችን መከላከል ስልጠና መስጠት የሚል ታቅዶ በዚህ ሩብ አመት ለ 70 ሴት እና ለ 78 ወንድ በድምሩ ለ148 ሰራተኞች ኤች.አይ ቪ. ኤድስ እና ተላለፊ በሽታዎችን እና የጾታ ጥቃት መከላከል የግንዛቤ የተፈጠር ሲሆን አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡

## አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት

## መረጃዎችን በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ተደራሽ ማድረግ

- በመረጃ ዴስክ አማካኝነት የውስጥና የውጭ ደንበኞችን በመልካም መስተንግዶ ተቀብሎ አስፈላጊ መረጃዎችን 100% ለመስጠት ታቅዶ በቅድሚያ የመረጃ ዴስክ ቢሮና ጊዚያዊ የእንግዳ መግቢያ ካርድ በክፍሉ ከተዘጋጀ በኋላ በቀን ዝቅተኛው 6 መካከለኛ 13 ከፍተኛ 36 ባለጉዳዮችን ተቀብሎ ወደሚፈልጉት ስራ አስፈፃሚ እንዲሄዱ የማድረግ ስራ የተሰራ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በዋናነት ፀረ ተባይና ማዳበሪያ ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘ ደንበኛ የተስተናገደበት ክፍል ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

- ጥራት ያላቸው መልዕክቶችን በማዘጋጀት በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች( በቴሌግራም፤ በፌስቡክ፤መረጃዎችን 100% ለተገልጋይ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ ባሉን ማህበራዊ ሚዲያዎች ተቋማችንን የሚመለከቱ ብቻ 33 የተለያዩ መልእክቶች ተዘጋጅተው በፌስ ቡክና በቴሌግራም እንዲጫኑ የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም ከተለያዩ ስራ አስፈፃሚዎች የተላኩልንን አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች በዌብ ሳይት ላይ እንዲጫኑ ለአይቲ ስራ አስፈፃሚ የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

## ሶሻል ሚዲያውን አይቶ ወደ ተግባር እንዲገባ የሚያስችል መልእክት መተላለፉ፣

- በተቋሙ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የለውጥ እንቅስቃሴ ለማሳየት 1 ጊዜ ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት ታቅዶ 1 ጊዜ ተሰጥቷል፡፡ 2 ጊዜ ብሮሸር አዘጋጅቶ ለማሰራጨት ታቅዶ 2 ጊዜ ተከናውኗል፡፡2 ጊዜ የዜና መጽሔት አዘጋጅቶ ለማሰራጨት ታቅዶ 1 ጊዜ ተከናውኗል 2ኛው የህትመት ስራ ይቀራል፡፡ 2 ጊዜ በቋሚ ዓምድ ለማስተላለፍ ታቅዶ 2 ጊዜ ተከናውኗል፡፡

## ኩነቶችን መምራትና ማስተባበር

- በተቋሙ የሚከናወኑ የተለያዩ ሁነቶችን በበላይነት በመምራት ሕብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲያገኝ የማድረግ ሥራ 100% ለመሥራት ታቅዶ በተለያዩ 37 የስልጠናና የውይይት መድረኮችን በበላይነት የማስተባበርና የመምራት ስራ ተሰርቷል፡፡
- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በ2 ጣቢያዎች ላይ በአካል በመገኘት የሕዝብ ግንኙነት ስራዎችን መስራትና ከመረጃ አያያዝና አጠቃቀም አኳያ ድጋፍ የለማድረግ ስራ ተሰርታል፡፡
- የሚዲያ አካላት ስለ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ እየተዘገቡ የሚወጡትን በየዕለቱ በመከታተልና ሞኒተር በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት በማድረግ ለአሉታዊ ጽሁፎች አስፈላጊውን የማስተካከያ መረጃ መስጠት ወይም እንዲሰጥ ለማድረግ ታቅዶ 100% ተከናውኗል፡፡

## ሌሎች የተከናወኑ ስራዎች

- የእጽዋት ግብአትና ምርት ጥራትና ደህንነት ምርመራ ስራዎች በባህሪያቸው ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የስራ ክፍሉን ለመደገፍና በተሻለ ደረጃ ለማጠናከር የሚያስችል ተጨማሪ የበጀት (ፋይናንስ) ምንጮችን ለማፈላለግ ይቻል ዘንድ የተለያዩ የፕሮጀክት ንድፈ-ሀሳብ ተዘጋጅተው ሀብት የማፈላለግ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከዚህ ቀደም ከስራ ክፍሉ ጋር በጋራ እየሰሩ ከሚገኙ አጋዥ ድርጅቶች በተጨማሪ በሁለተኛው ሩብ ዓመት ተጨማሪ ሀብት ለማፈላለግ ለሌላ ሁለት አጋዥ ድርጅቶች የሚቀርብ የሰነድ (Project Proposal) በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡

- በዓለም አቀፍ የዘር ጥራት ቁጥጥር ማህበር ISTA የሶስተኛ ወገን እውቅና ለማግኘት እየተደረገ ላለው ጉዞ ሂደቱ በሶስተኛ ምእራፍ ላይ ይገኛል፡፡ በሶስተኛው ምእራፍ በማህበሩ እንድናሟ ከተጠየቅናቸው መስፈርቶች መካከል ሰነድ የማዘጋጀት እና የማደራጀት ስራዎች ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ስራውም በአንደኛው ሩብ አመት ተጀምሮ በሁለተኛውም ሩብ አመት የቀጠለ ሲሆን በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ለማከናወን ከታቀደው አስር (10) የሰነድ ዝግጅት ስራዎች መካከል በአንደኛው ሩብ አመት በሁለት (2) ሰነዶች ላይ የመጀመሪያ ድራፋት የተዘጋጀ ሲሆን በሁለተኛው ሩብ አመት ደግሞ ሌላ ሁለት (2) ሰነዶች በመዘጋጀት ላይ ይገኛሉ፡፡
- በሁለገብ የላብራቶሪ ግንባታ ስራ ሂደት ላይ ክትትል የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡
- ለስራ ክፍላችን መጠናከር ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ ላይ በሚገኘው ATI በኩል የስራ ክፉሉን ስራ የሚያግዝ የአንድ (1) አማካሪ ባለሙያ ቅጥር ተከናውኗል፡፡
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ጉርድ ሾላ አካባቢ ባገኘው አዲስ ቦታ ላይ በአሁን ሰአት በእጽዋት ዘርፉ የምግብ ጥራትና ደህንነት ምርመራ/ፍተሻ አገልግሎት የሚሰጡ የሁለት (ማለትም፦ የኬሚካል ረሲጁ ምርመራ ላቦራቶሪ እና የማይኮቶክሲን ምርመራ ላቦራቶሪ) ላቦራቶሪዎች የመሳሪያ ተከላ ስራ እጅግ ውጤታማ በሆነ መልኩ ተጠናቋል፡፡
- በስራ ክፍሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ዘመናዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ አገልግሎቶችን ወደ ኦን-ላይን ዘዴ ለመቀየር የሚያስችሉ ስራዎች በመጨረሻ ምእራፉ ላይ ይገኛል፡፡
- ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ የእፅዋት ላቦራቶሪ የምርመራ መሳሪያዎች፣ የላቦራቶሪ ሶልቨንቶች፣ ሪኤጀንቶች፣ ኪቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእፅዋት ላቦራቶሪ ቁሳቁሶች የሚገቡባቸውን መስፈርቶች መሟላታቸው ተረጋግጦ ለ1 ድርጅት የጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ ተሰጥቷል፡፡

## አዲስ የኳረንቲን ጣቢያ ግንባታ

- ከDRIVE project ጋር በመሆን በጥናት በተለዩ ሁለት ቦታዎች  አዲስ የኳረንቲን ጣቢያ ግንባታ ለማከናወን በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ሞያሌ ወረዳ እና ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ቦርዴ ወረዳ የቦታ መረጣና ርክክብ ስራ ተከናውኗል፡፡

## የማር ሬዚጁ ሞኒተሪንግ ስራ

- በየዓመቱ ወደ አውሮፓ ገበያ የሚላክ የማር ምርት ላይ የሚደረገው የማር ቅሪት ምርመራ በዚህ አመት ለ16ኛ ጊዜ ከUNIDO Project በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሀገር አቀፍ የማር ናሙና ማሰባሰብና ከሀገር ውጪ ጀርመን ሀገር ባለው የINTERTEK ለብራቶሪ የማስመርመር ስራ ተጣናቆ የአናሊሲስ ስራና ዶክመት ዝግጅት እየተከናወና ይገኛል፡፡

- 24000ኪ/ግ የተፈጨ ቀንድና 158 ኪ/ግ ዝባድ የጥራትና ደህንነት ምርመራ በማድረግ ከምንም የበሽታ ምንጭ የፀዳ መሆኑን በማረጋገጥ የሰኒተሪ ሰርተፊኬት በመስጠት ከሃገር እንዲወጣ ተደርጓል፡፡
- በአመቱ እቅድ ሳይያዝ 130 የተለያዩ ዱር እንስሳትን አካላት የጥራትና ደህንነት ምርመራ በማድረግ ከምንም የበሽታ ምንጭ የፀዳ መሆኑን በማረጋገጥ የሰኒተሪ ሰርተፊኬት በመስጠት ከሃገር እንዲወጣ ተደርጓል፡፡
- 75 የዳክዬ ላባ ካርቶን ለጃኬት መስርያ የሚሆን የመግቢያ ፍቃድ ተሰቶ እንዲገባ ተደርጓል፡፡
- ለምርምር አገልግሎት በቀረቡት 224 የመኖ ናሙናዎች ላይ የጥራት ፍተሻ አግልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡
- ከላቦራቶሪ ምርመራ ሥራዎች የተረፉ የመድኃኒት ናሙናዎች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከማለፉ በፊት ከኦሮሚያ እንስሳት እና ዓሣ ሃብት ኤጀንሲ በተጠየቀው የድጋፍ ጥያቄ መሠረት በቦረና ዞን ለ6 ወረዳዎች በተወካያቸው በኩል በማስተላለፍ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ተችሏል፡፡

**ታቅዶ ያልተከናወነ**

- በላቦራቶሪ መሳሪያዎች መበላሸት ምክንያት የመኖ ጥራት እና የማር ጸረ ተባይ ቅርት ምርመራ ሥራዎች ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም።
- በዕቅድ የተያዙ የላቦራቶሪ ምርመራ ስነ-ዘዴዎችን ትክክለኝነት ማረጋገጫ እና የጸረ ተዋሲያ በጀርሞች መላመድ ሥራዎችን በላቦራቶሪ ግብዓት እና የባለሙያዎች እጥረት ምክንያት መፈጸም አልተቻለም።
- 2 የእንስሳት መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ጅምላ ንግድ ተቋማት ላይ ድህረ-ፈቃድ የኢንስፔክሽን ስራ ለማካሄድ ታቅዶ ተቋማቱ የጸጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢ በመሆኑ ነው፡፡

## የታዩ መልካም አጋጣሚዎች

- በሚሌ እንስሳት ከረንቲን በኩል የሚሰጠው አገልግሎት ተደራሽ መሆን

**ያጋጠሙ ችግሮች ናየተወሰዱ መፍትሔዎች**

**ያጋጠሙ ችግሮች**

- በፀረተባይ እና ማዳበሪያ ሕግ ማቀፎች ባብዛኛው በሂደት ላይ መሆናቸው ስራውን ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ መቸገር ፡፡
- በፀረተባይ እና ማዳበሪያ አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ያደረገ ቢሆንም የኔትዎርክ ችግር አልፎ አልፎ የሚያጋጥም በመሆኑን በፍጥነት ምላሽ መስጠት አንዳንዴ መከሰቱ፡፡
- በፀረተባይ እና ማዳበሪያ በመንግስት በኩል የሚገቡ ማዳበሪያዎች አንዳንድ ጊዜ የመግቢያ ፍቃድ ሳያገኙ የሚገቡበት መንገድ ስላለ መረጃዎቹን ለማግኛት መቸገር፡፡
- የላቦራቶሪ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እጥረት እና የመፈጸም አቅም ውስንነት መኖር፣

- የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት ግዥ መጓተትና የአቅርቦት እጥረት፣
- የላቦራቶሪ የቴክኒካል ባለሙያዎች አለመሟላት፣
- የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ብልሽት እና የጥገና መለዋወጫዎች አቅርቦት እጥረት፣
- የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ጥገና ባለሙያ አለመኖር፣
- 11 ኤክ/ቄራዎች የሚገኙ ሲሆን ያሉት የቄራ ሰርቪስ መኪና 4 ሲሆኑ በቂ ናቸው ብሎ መውሰድ አይቻልም አብዛኞቹ ለብዙ ዓመታት ያገለገሉና በተደጋጋሚ የሚበላሹ በመሆኑ ሥራ ለመግባትም ሆነ የመውጣት ሥርዓት ላይ ጫና አሳድሯል፡፡ በመሆኑም በተለይም ለሪቨር አክሺን፤ አልኑጃም፣ኤልፎራ፣ኢትዮ-ሚት መተሃራ፣ማዕረግ እና ለአቢሲኒያ ኤክ/ቄራ ሰርቪስ መኪና የሌላቸው ስለሆነ የሚመደብበት ሁኔታ ቢመቻች፣ በዘርፉ በኩል እገዛ ቢደረግ፣
- በየኤክ/ቄራ ኢንስ/ሰርተ/አገልግሎት ባለሞዎች ከጥቅማ ጥቅም ጋር በተያያዘ በየግዜው የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች አለመመለሳቸው፡፡
- የኤክ/ቄራዎች አጠቃላይ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማነስ እንዲሁም በገበያ የሚመራ የምርምርና ዕድገት አሰራር ሥርዓት አለመኖር ጋር ተያይዞ ቄራዎቹ ሲቋቋም ከነበራቸው የዕርድ አቅም (Designed Slaughtering Capacity) እና ዓመታዊ ዕቅዳቸው በታች አፈጻጸም ማስመዝገብ፣
- አንዳንድ ቄራዎች ደግሞ (አበርገሌ፣ ጅግጅጋ፤ ፍሪግሪኮ) ሙሉ በሙሉ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ኤክስፖርት ማቆማቸው፣
- በ ኤክ/ቄራ የውጪ ገበያን ለማስፋፋት በባልስልጣኑ ደረጃ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላቶች ጋር በሚፈለገው ደረጃ ተቀናጅቶ ያለመስራት፣
- በኤክ/ቄራ እንስሳት ምዝገባና ኋልዮሽ ሥርዓት ዝርጋታ ውስን መሆን፣
- በኤክ/ቄራ የሥጋ ጥራትና ደህንነት እና የቅሪት ምርመራና አቅም ማጎልበት ስራ ውስን መሆን፣
- በኤክ/ቄራ የውጪ/ተቀባይ አገራት የልምድ ልውውጥና የቅበላ መስፈርት ሥልጠና አለመኖር፣ ወዘተ፣
- በኤክ/ቄራ ለወጪ ገበያ የሚሆኑ የእርድ እንስሳትን በጥራትም ሆነ በብዛት በገበያ ላይ ያለማግኘት፣
- በኤክ/ቄራ የእንስሳት አቅርቦትና ግብይት ሰንሰለት ዕሴት በማይጨምሩ ደላሎች የተሞላና እንስሳት ዋጋ ከግዜ ወደ ግዜ እያሻቀበ መምጣቱ፡፡
- በእጸዋት ኳራንቲን የተጀመሩ የዲጅታላይዝ ስራዎች በተፈለገዉ ፍጥነት አለመሄዳቸዉ
- በእጸዋት ኳራንቲን የቁጥጥር ስርዓቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደካማ መሆን፣

- በእጸዋት ኳራንቲን ለአንድ መስኮት አገልግሎት የሲስተም እና ኢንተርኔት መቆራረጥ ስራ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ በማሳደሩ አልፎ አልፎ ለተገልጋዮች ላይ ቅሬታ መፈጠሩ፡፡
- በእጽዋት ኳራንታይንናሬጉላቶሪ እንዲሁም በስሩ ያሉ የስራ ክፍሎች በየክፍሉ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች በተለይም ፕሪንተርና የፕሪንተር ቀለም ያልተሟሉለት በመሆኑ የስራ ሂደቱ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሮዋል፡፡
- በእጸዋት ኳራንቲን የተቀባይ ሀገር መስፈርት በየጊዜው መቀያየርና እየጠበቀ መምጣት እና በዛዉ ልክ መስፈርቱን መሰረት ያደረገ ዕፅዋት ሬጉላቶሪ ስርዓት አለመጠናከር (በሰዉ ኃይል ፣ በማቴሪያል …)፡፡
- በእጸዋት ኳራንቲን ማሻሻያ የተደረገበት አዋጅ ለመጽደቅ መዘግየት፣
- በእጸዋት ኳራንቲን የዕፅዋት ድህረ መግባት (Post Entry Quarantine) ኳራንቲን ስርዓት አለመዘርጋት፣
- በእጸዋት ኳራንቲን ለዛይሌላ ሥራ በሚፈለግበት ጊዜ የፈሳሽ ናይትሮጅን አቅርቦት ማጣት እና ፈሳሽ ናይትሮጂን ሲገኝ ሆለታ ግብርና ባዮቴክኖሎጂ የሚደርስ የመኪና ችግር መኖሩ፡፡

- በእንስሳት ኳራንቲን በመንግስት በተወሰደው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርም ምክንያት የህገ ወጥ የቁም እንስሳት ንግዱ እየቀነሰ መምጣት
- በእንስሳት ኳራንቲን የኳራንቲን አገልግሎት የጨረሱ እንስሳትን ከአዳማ ወደ መዳረሻ ሀገራት በባቡር ማጓጓዝ መጀመሩ

**የተወሰዱ መፍትሔዎችና ምክረ ሀሳብ**

- በፀረተባይ እና ማዳበሪያ የስራ ክፍሉ ጊዜያዊ መስፈርቶችን እያዘጋጀ እና እያፀደቀ መሆኑ፣
- በፀረተባይ እና ማዳበሪያ የስራ ክፍሉ የኔትወርክ ችግሮችን ለመፍታት ለተወሰኑ ባለሞያዎች የገመድ-አልባ ራውተሮችን ለማግኘት ለክሮፕ ላይፍ ኢትዮጵያ ኮንሰብት ኖት በመፃፍ 8 ለማግነት ተችሏል፡፡

- በላቦራቶሪ የስራ ክፍል ክፍት የሥራ መደቦች ላይ የሰው ሃይል በዝውውር እና ኮንትራት ቅጥር እንዲሟላ ጥራት ተደርጓል፡፡
- በላቦራቶሪ የስራ ክፍል ከተለያዩ ተቋማት የባላሙያዎች ድጋፍ እና ትብብር በመጠየቅ እንዲሁም በተቋሙ ያሉ ሠራተኞች የተለያዩ ሥራዎችን ደርበው እንዲሰሩ በማድረግ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡
- የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት እጥረትን በተመለከተ በአስቸኳይ መሟላት የሚገባቸውን ከተለያዩ አቻ ተቋማት በትውስት እና በትብብር በመጠየቅ፤ እንዲሁም በጊዜ ሂደት መሟላት የሚገባቸውን ለተለያዩ የልማት አጋር ድርጅቶች የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲቻል ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ማቅረብ ተችሏል፡፡

- በኤክ/ቁራ የእንስሳት ዕጥረትን ለመቅረፍ ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር የተለያዩ አማራጮችን መተግበር።
- በኤክ/ቁራ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ሥራ ያቆሙ ቁራዎችን በቅርበት ችግራቸውን በመፈተሽ፣ በማገዝና በማብቃት ሥራ የሚጀምሩበት ሁኔታን ማመቻቸት።
- በእጸዋት ኳራንቲን ከፕሪንተር እና የፕሪንተር ቀለም ችግር ጋር ያለውን ችግር ለመቅረፍ ከሌሎች ክፍሎች ጋር በመተባበር ፕሪንተር ያላቸዉ ክፍሎች እንዲተባበሩን በማድረግ አንገብጋቢ የሆኑትን ስራዎች በመለየት ስራዎች እንዳይቋረጡ ለማድረግ ተሞክሯል።
- በእጸዋት ኳራንቲን የቁጥጥር ስርዓቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ደካማ የቴክኖሎጂ ስርዓት ቢኖርም ስራው እንዳይቋረጥ ባለው የመረጃ አቅርቦት ስራውን ማስቀጠል ተችሏል።
- በእጸዋት ኳራንቲን በአዲሱ አደረጃጀት ጠንካራ በሰው ሃይልና በቁሳቁስ የተደራጀ የዕፅዋት ኳራንቲን ጣቢያ እንዲኖር ለማድረግ ቢታቀድም ስራው እንዳይበደል/ለማስቀጠል ባለሙያዎች በዝውውር እንዲመጡና ቀደም ሲል ሲሰሩ የነበሩ ሰራተኞች ስራውን በውክልና ደርበው እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡
- በእጸዋት ኳራንቲን ማሻሻያ የተደረገበት አዋጅ እንዲጸድቅ በየጊዜው ክትትል ተደርጓል፡፡
- በእጸዋት ኳራንቲን የተቀባይ ሀገር መስፈርት መጥበቅን መሰረት ያደረገ ሀገራችን ዕፅዋት ሬጉላቶሪ ስርዓት ባይጠናከርም ለጊዜው በዚህ ወር ለባለሙያዎች እና የስራ ሃላፊዎች የአቅም ግንባታ ስልጠናና አሰራሩን ለማሻሻል የሚረዱ የመፍትሄ ሀሳቦች ተለይተዋል። እንዲሁም ለሁሉም ጣቢያዎች ወጥ የሆነ Phytosanitary certification አሰጣጥ እንዲኖር በደብዳቤ ማሳወቅ ተችሏል ።

**ቀጣይ የሥራ ትኩረት አቅጣጫዎች፡**

- የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ሥርዓት ትግበራ ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል፤
- የላቦራቶሪ የሰው ኃይል እንዲሟላ ማድረግ፤
- በላቦራቶሪ የግብዓት አቅርቦት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ግዥ ሥራዎችን እንድፈጠኑ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- በላቦራቶሪ በ2ኛ ሩብ ዓመት ታቅደው ያልተከናወኑ እና ከዕቅድ በታች የተከናወኑ ሥራዎች በ3ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ ውስጥ ተካተው እንዲፈጸሙ ማድረግ እንዲሁም የቀጣይ ሥራዎች በአግባቡ እንዲፈጸሙ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤
- ከላቦራቶሪ የሚወጡ ኬሚካሎች እና ሪኤጀንቶች እንዲሁም ተያያዥ ቁሳቁሶችን በሥራ ከባቢ እና በተቋሙ ሠራተኞች ላይ የጤና ስጋት እንዳያደርስ ማስወገድ።
- በላቦራቶሪ ከድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች እና ግብርና ሚ/ር ፕሮጀክቶች ጋር የሚሰሩ የትብብርና ድጋፍ ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል

- የእጸዋት ላብራቶሪዎችን ለማጠናከርና አቅማቸውንም ለማሳደግ የተጀመሩትን ሀብት የማፈላለግ ስራዎች አጠናክሮ መቀጠል፡፡
- የእጸዋት ላብራቶሪዎችን በአዲስ መልክ ለማቋቋምና ለማደራጀት የታሰቡ ደረጃቸውን የጠበቁ ለሶስተኛ ወገን እውቅና ብቁ የሆኑየማቋቋምና የማደራጀት ስራዎችን ማጠናከር፡፡
- የእጸዋት ላብራቶሪው ከደንበኞች የሚነሱ አስተያየቶችን በመቀበል እንዲሁም የሌሎች ሀገራት ልምድ በመቅሰምና በመቀመር የእጽዋት ግብአትና ምርት ጥራት ምርመራ ስራን ማሻሻል እና የተቀላጠፈ ማድረግ፤ በተጨማሪም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ለምርመራ ስራው አስፈላጊ የሆኑ ማንዋሎችን፣ ጋይድላይኖችን እና ደረጃዎችን ማሻሻል እና አዳዲስ ማዘጋጀትና ማውጣት፡፡
- የእጸዋት ላብራቶሪው በስራ ክፍሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ዘመናዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ አገልግሎቶችን ወደ ኦንላይን ዘዴ ለመቀየር በአንደኛውና በሁለተኛው ሩብ አመት የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል፡፡

## 4. የ2017 የ2^ተኛ^ው ሩብ ዓመት የበጀት አፈጻጸም

| የበጀት ዓይነት | መለኪያ | ለ2017 የተፈቀደ በጀት | የ6 ወራት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንዉን | አፈጻጸም በመቶኛ |
| መደበኛ | በብር | 194,047,382.20 | 109,803,554.36 | 78,196,985.44 | 71.2% |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ካፒታል | በብር | 1,000,000.00 | 1,000,000.00 | 1,000,000. 00 | 100% ዝውውር ተደርጓል |
| ድምር | | 194,047,382.20 | 109,803,554.36 | 78,196,985.44 | 71.2% |

## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 2ተኛ ሩብ ዓመት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት በቁልፍ አመልካች

| ቁልፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ የ2016 አፈጻጸም | የ2017 ዕቅድ | የ2ተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በዚህ ሩብ ዓመት | | | እስከዚህ ሩብ አመት | | |
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
| ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ | | | | | | | | | |
| ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ | ቶን | 78,343.00 | 111,437.00 | 17,850 | 8016 | 44.9 | 28549 | 33145 | 100+ |
| ጥራቱ የተረጋገጠ የአፈር ማዳበሪያ | ቶን | 2,510,360 | 2,339,971 | 562,779 | 410714 | 73 | 1,125,558 | 1772497 | 100 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 198 | 225 | 52 | 66 | >100 | 127 | 177 | >100 |
| በአከባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ | የሰነድ ቁጥር | 1 | 2 | 1 | | | 1 | 1 | 100 |
| **ጤንነታቸዉ ጥራትና ደህንነታቸው ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ዉስጥ ገቢያ የቀረቡ እፅዋት ምርቶች** | | | | | | | | | |
| ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች | ቶን | 875,313 | 860,000 | 215,000 | 228834 | 106.4 | 430,000 | 456,477 | 106 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች | ቶን | 39,643 | 60,000 | 15,000 | 47354 | ›100 | 30,000 | 55266 | ›100 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 638 | 838 | 270 | 187 | 93.5 | 570 | 387 | 68 |
| በአከባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ | ሰነድ በቁጥር | 1 | 2 | | | | 1 | 1 | 100 |
| **የዕጽዋት ዝርያ ጥበቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር** | | | | | | | | | |
| በምርምር ቀርበው የተገመገሙ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎች | ቁጥር | 164 | 120 | 60 | 73 | ›100 | 80 | 85 | 106 |
| በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ የአገር ውስጥ ዘር | ኩንታል | 829,197 | 1,527,905 | | | | | 161837 | |
| በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ ከውጭ አገር የገባ ዘር መጠን ውስጥ ለላብራቶሪ የቀረበ የናሙና ብዛት | ቁጥር | 303 | 250 | 70 | 58 | 82 | 120 | 166 | >100 |
| በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ ከውጭ አገር የሚገባ ዘር | ኩንታል | 617, 640 | 509,603 | 142,688 | 82951.5 | 58.13 | 244,608 | 146759 | 60 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 30 | 30 | 15 | 19 | >100 | 15 | 34 | >100% |
| ጥራቱ በላብራቶሪ ተረጋግጦ ከውጭ የገባ የዕፀዋት ዘር ናሙና | በቁጥር | 171 | 250 | 70 | 98 | 140 | 120 | 206 | 171.66 |
| **የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ** | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ደህንነቱ ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ስጋና ተረፈ ሥጋ | በቶን | 18,647.53 | 15,000 | 3,750 | 7221.25 | >100 | 7,500 | 9512.4 | ›100 |
| ዓለም አቀፍ የሥጋ ደህንነት እና ጤንነት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት መስጠት | ጥራዝ ብዛት | 3000 | 3000 | 3000 | 4211 | 140 | 3000 | 4211 | 140 |
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የስጋና ተረፈ ስጋ አምራች ተቋማት | በቁጥር | 12 | 15 | 15 | | | 15 | | |
| ጥራቱና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ የተረጋገጠ የእንስሳት ምርት ናሙናዎች | ቁጥር | 480 | 600 | 180 | | | 300 | **96** | **80%** |
| ለኮመርሻል የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ | በቁጥር | 55 | 71 | 35 | 25 | 71 | 35 | 25 | 71 |
| በኤክስፖርት ቄራና ተረፈ ስጋ ማቀናበሪያ ፋብሪካዎች ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት | በቁጥር | 4 | 4 | 2 | 2 | 100 | 2 | 2 | 100 |
| በእንስሳት ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | ቁጥር | 56 | 56 | 14 | 14 | 100 | 28 | 28 | 100 |
| ለእንሰሳት ምርት ጥራትና ጤንነት ደህንነት ላይ ለሚሰሩ ኢንስፔክተሮችና ሰርተፊኬሽን ባለሞያዎች እያደገ የሚሄድ የዓቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት፣ | የሠልጣኝ ብዛት | 120 | | | | | 60 | 61 | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች** | | | | | | | | | |
| **ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ የቁም እንስሳት** | **ቁጥር** | 256,809 | 390,000 | 100,000 | 171022 | 100 | 195,000 | 280060 | >100% |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ የለማ እንቁላል | ቁጥር | 4,535,602 | 546,000 | 136,000 | 86000 | 100 | 272,000 | 342000 | >100% |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ሰምና ማር | ቶን | 145 | 450 | 110 | 61.5 | 56 | 220 | 118.5 | 56% |
| ጥራቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ቆዳና ሌጦ | ቁጥር | 3,060,464 | 3,572,450 | 897,450 | 1990204 | >100 | 1,785,450 | 2913765 | >100% |
| ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል | ቁጥር | 889,637 | 689,090 | 173,000 | 154680 | 89.4 | 345,000 | 251810 | 73% |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ የተሻሻለ ዳልጋ ከብት | ቁጥር | 120 | 275 | 68 | 198 | ›100 | 138 | 298 | >100% |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ አባላዘር | ዶዝ | 59,872 | 12,000 | 3,000 | 91555 | >100 | 6,000 | 96955 | >100 |
| **ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት** | | | | | | | | | |
| ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት | በቶን | 3043 | 2,850 | 712.5 | **706** | **99.08** | 1425 | **1854** | **130** |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተገምግሞ፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ የተመዘገበ የእንስሳት መድሃኒት | በቁጥር | 94 | 75 | 19 | **72** | **›100** | 37 | **104** | **100** |
| የመድሃኒት ናሙዎችን ላይ የተካሄደ የጥራት፣ ደህንነት አና ፈዋሽነት የላቦራቶሪ ምርመራ | በቁጥር | 305 | 300 | 75 | | | 150 | **75** | **50** |
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት | በቁጥር | 313 | 375 | 94 | **138** | **>100** | 187 | **202** | **›100** |
| የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 536 | 629 | 157 | **103** | **65.6** | 314 | **239** | **76** |
| **ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ** | | | | | | | | | |
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ መኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት | በቁጥር | 310 | 461 | 122 | 131 | ›100 | 352 | 284 | 80.68 |
| በእንስሳት መኖ እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 247 | 313 | 83 | 83 | 100 | 155 | 138 | 89 |
| ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ መኖ እና የመኖ ግብዓት | ቶን | 6273.218 | 5,500 | 1375 | 2408.8 | ›100 | 2750 | 5184.15 | >100 |
| የመኖ እና የመኖ ጥሬ ግብዓት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የጥራት እና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ | ቁጥር | 8 | 130 | 35 | 38 | ›100 | 65 | 68 | 100 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ የተመረተ የተቀነባበረ መኖ እና የመኖ ግብዓት | ቶን | --- | 113651 | 56,826 | 147,493 | >100 | 85,227 | 149,917 | >100 |
| **ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የዕጽዋት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት** | | | | | | | | | |
| **የተዘረጋ የእንስሳት የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት (ISO/IEC 17025) ትግበራ** | **ቁጥር** | 16 | 14 | | | | | | |
| እውቅና/አክሪዲቴሽን የተገኝባቸው የእንስሳት የላቦራቶሪ ምርመራ ስነ ዘዴዎች | ቁጥር | | 20 | | | | | | |
| በመድኃኒት ምርት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ መጠን | ቁጥር | | 300 | 150 | 199 | 100 | 150 | 199 | 100 |
| በመኖ ምርት ናሙናዎች ላይ የተከናወነ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ መጠን | ቁጥር | | 130 | 65 | 68 | 100 | 65 | 68 | 100 |
| በእንስሳት ምርት ናሙናዎችላይ የተከናወነ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ መጠን | ቁጥር | | 600 | 300 | 411 | 100 | 300 | 411 | 100 |
| የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ በማሳደግ የተገኘ የላቦራቶሪ ምርመራ እውቅና ወይም አክሪዲቴሽን | ቁጥር | | 16 | 16 | 16 | 100 | 16 | 16 | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| የሰው ሃብት ሙላት | | | | | | | | | |
| በቅጥር | በቁጥር | | 27 | | | | 7 | 2 | 28.57 |
| በተለያዩ ዘዴዎች የሚቀርቡ የማስረጃ ጥያቄዎችን ማስተናገድ | በመቶ ኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ከጡረታ ማስከበር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራትን ማከናወን | በቁጥር | | 10 | 2 | 5 | 100 | 2 | 5 | 100 |
| ግልፀኝነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት | በመቶ ኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ለአመራርና ለሠራተኞች የሚሰጡ ሥልጠናዎች ማሰደግ | በቁጥር | | 33 | 11 | | | 11 | | |
| ዘመናዊ የሠራተኛ መረጃ እና የሪክርድ ሥራ | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሰራተኛ እርካታን በማሳደግ ፍልሰትን መቀነስ | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ሪፖርት ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ-መልስን ማሻሻል | | | | | | | | | |
| የተሻሻለ የእቅድ ፣ ሪፖርት ዝግጅት ግምገማና የመረጃ አስተዳደር | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ እቅድና ሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት | ሰነድ | 10 | 10 | 2 | 2 | 100 | 6 | 6 | 100 |
| የክትትልና ግምገማ አሰራር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ | በጊዜ | 8 | 8 | 2 | 2 | 100 | 4 | 4 | 100 |
| የበጀት እና እቅድ አፈጻጸም ትግበራ ክትትልና ግምገማ ማድረግ | በጊዜ | 12 | 12 | 3 | 3 | 66.6 | 6 | 6 | 100 |
| ስትራቴጂካዊ መረጃ አያያዝ ሥርዓትን ማዘመን | በመቶ ኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቶችን ስራዎችን የመከታተልና የመደገፍ ስራዎች | ሰነድ | | 1 | | | | 1 | 1 | 100 |
| የፋይናንስና ግዥ አስተዳደር ማሻሻል | | | | | | | | | |
| የተመደበውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ነቀፊታ ያለበትን የኦዲት ግንኝትን መቀነስ | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የመንግስት የኤሌክትሮኒክስ ክፍያን በመቀጠም ወቅቱን የጠበቀ እና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት | ሲስተ ም | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የመንግስት የኤሌክትሮኒክስ ግዣ ሥርዓትን በመጠቀም ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው የግዠ አገልግሎት መስጠት | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| መሠረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ኤሌክትርኒክስ የንብረት ምዝገባ ቁጥጥር ሥርዐትን በመጠቀም የንብረት አያያዝን ዘመናዊ እና ቀልጣፋ ማድረግ | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የመኪና ሥምርሪት ሥራን መከታተል እና መተግበር | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ለውጤታማነትን ማሻሻል | | | | | | | | | |
| የተመሠረተ የመረጃ ሥርዓት | | | | | | | | | |
| የኦንላይን አንድ መስኮት አገልግሎት ሲስተምን ማስተዳደር | በመቶ ያ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የኢሰርቪስ ሲስተሞችን ማስተዳደር | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኤሌክትሮኒክ ግዢ እና የኢፍሚስ ሲስተሞችን ማስተዳደር | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የኮምፒውተርና የኔትዎርክጥገና ስራ ማከናወን | በቁጥር | 14 | 25 | 5 | 5 | 100 | 5 | 5 | 100 |
| ተቋማዊ የሪፎም ሥርዓት በመጠቀም የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ | | | | | | | | | |
| የተገልጋይን እርካታ ማሳደግ | በመቶ ኛ | 83 | 85 | 84 | 83 | 98.80 | 84 | 83 | 98.80 |
| በተቋሙ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መፍታት | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ተቋማዊ ካይዘን ሥርዓት መተግበር | በመቶ ኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ተግባራዊ የተደረገ የህግ ማዐቀፍ | | | | | | | | | |
| ተዘጋጅቶ በሚቀርበው ረቂቅ ሰነድ ላይ የህግ አስተያየት መስጠት | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የባለስልጣኑን አዋጅ ደንብና መመሪያ ላይ | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ግንዛቤ መስጠት | | | | | | | | | |
| ህገ ወጥ የግብርዓ ግብዓት ንግድና ዝውውርን በሚፈጸምባቸው ቦታወች ላይ ቁጥጥር ማድረግ | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ተዘጋጅቶ በሚቀርበው ረቂቅ ሰነድ ላይ የህግ አስተያየት መስጠት | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት | | | | | | | | | |
| መረጃዎችን በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ተደራሽ ማድረግ | በቁጥር | 38 | 38 | 10 | | | 14 | | |
| ሶሻል ሚዲያውን አይቶ ወደ ተግባር እንዲገባ የሚያስችል መልእክት መተላለፉ፣ | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ኩነቶችን መምራትና ማስተባበር | በመቶ ኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስነ ምግባርና የፀረ ሙስና | | | | | | | | | |
| የሥነ ምግባር ውጤታማነት ግንዛቤ ማሳደግ | የመድረክ ቁጥር | 14 | 14 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| የሙስና ተጋላጭነት ስጋትን መቀነስ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የሙስና መረጃ አስተረዳዳር ውጤታማነትን ማረጋገጥ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ማህበራዊ አካታችነትና የሴቶች ተጠቃሚነት | | | | | | | | | |
| ወደ አመራር የመጡ ሴት ሰራተኞች አቅም ማሳደግ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የማህበራዊ አካቶ ትግበራን በአካባቢ  እና ማህበራዊ ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ለመቀነስ  ተግባራዊነቱን መከታተል | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| በባለስልጣኑ የሴቶች፣ ህጻናት፣ወጣቶችና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |